የገፀባህሪያት አሳሳል
በየጠፍ ከዋክብት ረጅም ልብ ወለድ

በ
ካቢኒ መኮንን

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል
ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

የጥናቱ አማካሪ
አቶ አየለ ፍቅሬ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2001 ዓ.ም

# የገፀባህሪያት አሳሳል
# በየጠፍ ከዋክብት ረጅም ልብ ወለድ

በ
ካቢኒ መኮንን

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል

ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2001 ዓ.ም

## አበርክቶ

በፍጽም አገር ፍቅር አገራቸውን ከውጭ ወራሪ የታደጉና ለአገራቸው ዳር ድንበር በእውነት ስለእውነት ስለአለፉ ጀግና ኢትዮጵያዊን መታሰቢያ ይሁንልኝ፡፡

## ምስጋና

- በቅድሚያ የዓለም ንጉስ መቸር መስጠት ለማይታክተው አምላክ እግዚአበሔር ምስጋና ይድረሰው። አሜን!!
- ይህንን የመመረቂያ ፁሒፍ በትዕግስትና በትጋት በፍፅም ትህትና በማረም በማስተካከል ጠቃሚ ሀሣብ በመስጠት ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለአቶ አየለ ፍቅሬ ምስጋናዬ የላቀ ነው።
- ለዚህ ጥናት ርዕሰ በሆነው መጽሐፍ እንድሰራ እገዛ ላደረጉልኝ መምህሬ ለአቶ ገዛኸኝ ጌታቸው እንዲሁም በጎ ፈቃዳቸውን ሁሉ ላልተለየኝ ጓደኞቼ ተካ፣ ከሪማ፣አብዱ ምስጋናዬ የላቀ ነው።
- በመጨረሻም ይህንን ፅሑፍ በመተየብ በማስተካከል ለረዱኝ ለኪዳነምህረት ፎቶ ስትዲዮ ሠራተኞች በሙሉ በተለይም ለወ/ሪት አዜብ አሻግሬ ምስጋናዬ ወደር የለውም።

## ማውጫ

አርዕስት

ገጽ

**1. መግቢያ**

የጥናቱ ዳራ----------------------------------------------------------1

የጥናቱ ዓላማ ------------------------------------------------------ 2

የጥናቱ ጠቀሜታ---------------------------------------------------- 2

የጥናቱ ገደብ-------------------------------------------------------- 2

የጥናቱ ዘዴ--------------------------------------------------------- 3

የጥናቱ አደረጃጀት-------------------------------------------------- 3

**2. ክለሳ ድርሳናት**

የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት--------------------------------------------4

የንድፈ ሃሣባዊ መሠረት -----------------------------------------5

የገፀባህርይ ምንነት---------------------------------------------5

የገፀባህርይ አሳሳል -----------------------------------------6

የገፀባህርይ አሳሳል ደረጃዎች--------------------------------7

2.2.3.1 ውጫዊ ገጽታ------------------------------------9

2.2.3.2 ውስጣዊ ገጽታ-----------------------------------9

የገፀባህርይ አቀራረብ ዘዴዎች ----------------------------9

የገፀባህርይ አይነቶች-------------------------------------10

3. የገፀ ባህርያት አሣሣል በ <u>የጠፍ ከዋክብት</u> (1999) ረጅም ልቦለድ

የ <u>የጠፍ ከዋክብት</u> ታሪክ በአጭሩ----------------------------------11

የዋና ገፀባህርይ አሳሳል---------------------------------------------13

3.2.1 አካላዊ አሳሳል--------------------------------------------------13

የሴማዊት አካላዊ አሳሳል----------------------14
3.2.1.2የጄነራል ፍራንካና የምክትል
ጄነራል ሲልቪዮ አካላዊ አሳሳል-----------------15
3.2.1.3 የአቶ በሼ አካላዊ አሳሳል------------------------16
3.2.1.4 የተፈሪ አካላዊ አሳሳል---------------------------16
3.2.1.5 የኪዳኔ አካላዊ አሳሳል----------------------------18
3.2.2 ህሊናዊ አሣሣል-------------------------------------------------18
3.2.2.1 የሴማዊት ህሊናዊ አሳሳል-----------------------19
3.2.2.2 የጄነራል ፍራንኮ ህሊናዊ አሳሳል----------------23
3.2.2.3 የምክትል ጄነራል ሲልቪዮ ህሊናዊ አሳሳል----25
3.2.2.4 የአቶ በሼ ህሊናዊ አሳሳል-----------------------28
3.2.2.5 የተፈሪ ህሊናዊ አሳሳል--------------------------32
3.2.2.6 የኪዳኔ ህሊናዊ አሳሳል--------------------------35
ማጠቃለያ--------------------------------------------------------------38
- ዋቢ ጽሑፎች

## 1. መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ልቦለድ ድርሰት ደራሲው መሠረታዊ የሆኑ የሰው ልጅ ጉዳዮችን ማለትም ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ እሴቶችን መሠረት አድርጎ ለአንባቢ አንዳች ትምህርት ሊሰጥ በሚችል መንገድ የሆነውን፤ የተደረገውን ወይም ቢሆን የሚለውን ምኞቱን ወይም ፍላጎቱን ሥነ- ጽሑፋዊ ለዛ ሰጥቶ የሚያቀርብበት የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው፡፡

ይህ ሲባል ግን የተፃፉ ልቦለዶች ሁሉ ሁልጊዜ ለማስተላለፍ የተፈለጉትን መልዕክት በጥሩ ሁኔታ ያስተላልፋሉ ማለት አይደለም፡፡

አንድ ልቦለድ ድርሰት የታለመለትን ግብ እንዳይመታ ሊያደረጉት ከሚችሉት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ባለታሪኮቹ የሆኑት ገፀ ባህሪያት በድርሰት ውስጥ በተገቢው መልክ ተስለው ያለመገኘታቸው ነው፡፡ ምንም እንኳ አንድ የድርሰት ሥራ በሁሉም የልቦለድ አላባውያንና ዘዴዎች ምሉዕ ቢሆን በገፀ ባህሪያት አሳሳል ረገድ ህፀጽ ቢገኝበት በሃያስያን ዘንድ ጎደሎ መባሉ አይቀሬ ነው፡፡

በእርግጥ አንድ ፀሐፊ ልቦለድ ድርሰቱን ጽፎ ለአንባቢያን ሲያቀርብ አንባቢያንም አንብበው ሲጨርሱ ልቦለድ ድርሰቱን እንዴት አያችሁት? ተብለው ቢጠየቁ አሳዛኝ ወይም አስደሳች፤ አልያም ልብ ሰቃይ ነው አይደለም፣ በሚል በድፍኑ ጅምላ ሐሳባቸውን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ሃያሲ ግን እንዲህ አይደለም፡፡ "እንዲህ ነው" ብሎ ለሚሰጠው እያንዳንዱ አስተያየት ምክንያት አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንድ የልቦለድ ድርሰትን አንብቦ አስተያየት ለመስጠት ሲነሳ ለልቦለዱ መገኘት እንደ ድርና ማግ ሆነው የሚያገለግሉትን አላባውያንን ጨምሮ እስከ የልቦለድ ዘዴዎች ከዚያም ሲያልፍ ከልቦለዱ ርዕስ እስከ የሽፋን ገጽ ስዕል ድረስ በጥልቀት ይመለከታል፡፡ ከዚያም በሚችለው መጠን በአንዱ ወይም በሌላው የድርሰቱ አካል ላይ ጅምላ አሊያም ንጥል ሂስ ይሰጣል፡፡ የዚህ ጥናት አጥኚም <u>የጠፍ ከዋክብት</u> በተባለው ታሪክ ጠቀስ ረጅም ልቦለድ ላይ ከአላባውያን አንዱ በሆነው ገፀ ባህሪ በተለይም በገፀ ባህሪ አሳሳል ላይ ትኩረት በማድረግ ድርሰቱን ለመፈተሽ ይሞክራል፡፡

ሽንቁጥ አየለ በልቦለድ ደራሲነት ወደ መድረክ ብቅ ያለው በ1999 ዓ.ም የጠፍ ከዋክብት በተባለው ረዥም ልቦለድ አማካኝነት ነው፡፡ ደራሲው ልቦለድን ለተደራሲ ማቅረብ የመጀመሪያው እንደመሆኑ መጠን በገፀባህሪይ አሣሣል ረገድ ጠንካራና ደካማ ጐኖቹን ለመመልከት ችያለሁ፡፡ ስለሆነም ለዚህ ጥናት አነሣሽ ምክንያቴ ይህንን ድክመት መተንተን ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያቴ ስለመፀሐፉ ከዚህ ቀደም ምንም ዓይነት ጥናት አለመደረጉ ሲሆን ሶስተኛና የመጨረሻው ምክንያቴ የሥነ-ፁሑፍ ተማሪ እንደመሆኔ መጠን በየጠፍ ከዋክብት ልቦለድ ውስጥ የሚገኙትን ገፀባህሪያት እንዴት ተቀርፀዋል የሚለውን ለማጥናት ወሰንኩ፡፡

1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አላማ **የጠፍ ከዋክብት** በተሰኘው ልቦለድ ውስጥ ያሉትን ገፀባህሪያት ምንነት፣ አሣሣል፣ አቀራረብ ዘዴዎችና አይነቶችን የተለያዩ ምሁራንን ንድፈ ሃሣባዊ መሠረቶች በመመርኮዝ ጥንካሬና ድክመቱን ማሳየት ነው፡፡

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

**የጠፍ ከዋክብት** በተሰኘው ረዥም ልቦለድ ድርሰት ላይ የተደረገው የገፀ ባህሪያት አሳሳል ብዙ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ብሎ አጥኚው ያምናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ይህ ረዥም ልቦለድ ድርሰት ሊያስተላልፍ ከፈለገው ማኀበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ አንፃር የገፀ ባህሪያት አሳሳል ላይ በሚቀርበው ትንታኔ አንባቢ በመስኩ ያለውን የዕውቀት ክፍተት መሙላት ያስችለዋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የዚህ ጥናት ትኩረት የገፀ ባህሪያት አሳሳል ላይ ትንተና መስጠት ስለሆነ ለሌሎች አጥኚዎች በመነሻነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

1.4 የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ **የጠፍ ከዋክብት** የተባለውን ረጅም ልቦለድ ድርሰት ከሁሉም የልቦለድ አላባውያን ወይም ዘዴዎች አንፃር ለመመዘን የሚሞክር አይደለም፡፡ ከርዕሱ ለመረዳት እንደሚቻለው ትኩረቱ ከልቦለድ አላባውያን አንዱ በሆነው ገፀባህሪ ላይ ብቻ ይሆናል እንጂ፤ ከዚህ አልፎ ልቦለዱ በእያንዳንዱ የረጅም ልቦለድ አላባውያን ሲመዘን የሚኖረውን ድክመትና ጥንካሬ ይህ ጥናት በጥልቀት አያትትም፡፡

## 1.5 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ መሠረት የሚያደርገው ገላጭ ምርምር ሲሆን የገጽ ንባብ ትንተና ስልት ላይ በመመስረት በተመረጠው ልቦለድ ውስጥ የገፀባህርያትን አሳሳል ለመዳሰስ ይሞክራል፡፡ስለ አሰራር ሂደቱም በቅድሚያ ልቦለዱን በተደጋጋሚ በማንበብ የገፀ ባህርያቱን አሳሳል መተንተን እና ለልቦለዱ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ለማሳየት ይሞክራል፡፡

## 1.6 የጥናቱ አደረጃጀት

የዚህ ጥናት አደረጃጀት በአብዛኛው የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የሚረዱ በታተሙ ረጅም ልቦለድ አላባውያን መርጃ መጽሐፍቶች፣ የመመረቂያ ጽሑፎች እና ስለ ገፀ ባህርያት አሳሳል በተገኙ መረጃዎች መሠረት የሚከናወን እና የሚደራጅ ነው፡፡

ጥናቱ ለአሠራር ያመች ዘንድ በሶስት ምዕራፎች ተከፍሏል፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ገደብ፣ የጥናቱ ዘዴ እና የጥናቱ አደረጃጀት ይገኙበታል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝትና ንድፈ ሃሣባዊ መሠረትን ሲይዝ፡፡ ሶስተኛው ምዕራፍ ደግሞ የጥናቱ ዋና ትኩረት የሆነውን የገፀ ባህሪይ አሳሳል ትንተናን ይዟል፡፡ በመጨረሻም ማጠቃለያ፣ ዋቢ መጽሐፍት፣የመመረቂያ ጽሑፎች፣ ተካተዋል፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ይህን ጥናት ለማድረግ ከእኔ ጥናት ርዕስ ጋር የተሻለ ቅርበት ያላቸውን በርካታ የዲግሪ ሚሚያ ፅሁፎች ለመቃኘት ሞክሪያለሁ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የደሣለኝ አሰፋ /1992 ዓ.ም/"ሥነ ጽሑፋዊ ሂስ በኢቫንጋዲ እና ከቡስካ በስተጀርባ"አንዱ ነው፡፡ ደሳለኝ በሁለቱ መጽሐፎች ላይ ሥነ ጽሑፋዊ ሂስ በማድረግ የመጽሐፎቹን ጥንካሬና ቀርነት አሳይቶ በድክመቱ ላይ የመፍትሄ ሃሳብ መጠቆምን አላማው አድርጎ ተነስቷል፡፡ በዚህም መሠረት የገፀባህሪያትን አሣሣል ከባህሪ ዘላቂነትና ታዓማኒነት አንፃር እንዲሁ የደራሲውን የቋንቋ አጠቃቀም ለመገምገም ሞክሯል፡፡አጥኚው ከተነሳበት ዓላማ አንፃር በገፀ ባህሪም ሆነ በደራሲው የቋንቋ አጠቃቀም ላይ የታዩትን ድክመትና ጥንካሬ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ይ¦ም በመሆኑ የተነሳበትን ዓላማ አሳክቷል ለማለት ይቻላል፡፡

ይህ ጥናት ደሳለኝ ካጠናበት ልቦለድ የተለየ መሆኑና የደራሲውን የቋንቋ አጠቃቀም አለመመልከቱ ልዩ ቢያደርገውም በገፀ ባህሪያት አቀራረጽ ላይ በትኩረት ሂሳዊ ምዘና መስጠቱ ከደሳለኝ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

ሌላው ከኔ ጥናት ጋር ቅርበት ኖሮት ያየሁት ዮሴፍ ጌትነት /በ(1993)ዓ.ም/ "ሽፍትነት በጥቁር ደም ልቦለድ የገፀ ባህሪያት አቀራረጽ" በሚል የሰራው ዲማጽ ነው፡፡ አጥኚው በመጽሐፉ ውስጥ የሽፍትነት ገፀ ባህሪያት አቀራረጽ ዘላቂነትና ታዓማኒነትን ማሳየት አላማው በማድረግ ጥናቱን ይጀምራል፡፡ ነገር ግን ከገፀ ባህሪያቱ ጋር በማያያዝ ጭብጥን፣ የትረካ አንፃርና መቼትንም ሲነካካ ይስተዋላል፡፡ ይህም ደግሞ አጥኚው ከተነሳበት ዓላማ አንፃር ያለበትን ቀርነት የሚያመለክት ሲሆን፣ ከዚያም በተጨማሪ ዳራ ተሰጥቶት ሣለ በቂ ዳራ አልተሰጠውም ማለቱ እንደድክመት ቢታይም ከዚያ ውጭ ግን የገፀባህሪያቱን አሣሣል ደካማና ጠንካራ ጐኑን ማሣየት መቻሉ በጎ ጐኑ ነው፡፡

ይህ ጥናት ከዮሴፍ የሚለየው ካጠናበት ልቦለድ የተለየ መሆኑ በመቼት፣ በትረካ አንፃር፣ እንዲሁም በጭብጥ ዙሪያ ትንተና አለመስጠቱ ነው፡፡ የገፀ ባህሪያቱን አሣሣል በተመለከተ ዘላቂነትን፣ ተዓማኒነትን፣ የገፀባህሪይ ውጫዊና ውስጣዊ መልክ አቀራረፅን በልቦለድ ውስጥ መተንተኑ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሣስለዋል፡፡

ሽባባው ወሌ በ(1976) ዓ.ም "የገፀባህሪይ፣ የግጭትና ጭብጥ ትንተና በአደፍርስና ከአድማስ በሻገር" በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናት በሁለቱ መጽሐፎች

ያሉትን ገፀባህሪያት፣ ግጭትና ጭብጥ ትንተና ንፅፅራዊ በሆኑ መልኩ ተንትኖ ማሳየትን አላማ አድርጐ ተነስቷል፡፡

በዚህም መሠረት ሶስቱንም የልቦለድ አላባዎች የተለያየ ንድፈ ሃሳቦችን በመጠቀም ለመተንተን ሞክሯል፡፡ “የገፀ ባህሪ ትንተና” ብሎ ባስቀመጠው ንዑስ ርዕስ ስርም የሁለቱን መጽሐፎች ዋና ገፀ ባህሪያትን በመውሰድ ትንተና ሰጥቷል፡፡ ስለዚህም የዚህ ዲማጽ ፀሐፊ ከተነሳበት አላማ አንፃር የሰጠው ትንታኔ ግቡን መትቷል የሚያሰኝ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ይህ ጥናት ከሽባባው የሚለየው ያጠናባቸው ልቦለድ መጽሐፎች ከእኔ የጥናት መጽሐፍ ከመለየታቸውም ባሻገር ሁለት መጽሐፍትን በንጽጽር ማቅረቡ እንዲሁም የግጭትና የጭብጥ ትንተናን አክሎ ማቅረቡ ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ደግሞ የገፀ ባህሪ ትንተና መስጠቱ ነው፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ውስጥ ያካተትኳቸውና የዳሰስኳቸው የድግሪ ሚሚያ ጽሑፎች ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው የገፀ ባህሪያት አሳሳል ላይ ትንተና ማድረግና ሂስ መስጠታቸው ነው፡፡ እኔም በዚህ የጥናት ጽሑፌ ሽንቁጥ አየለ ታሪክ ጠቀስ ያለው <u>የጠፍ ከዋክብት</u> መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ገፀ ባህሪያት አሳሳል ሂሳዊ በመሆነ መልኩ ለመተንተን እሞክራለሁ፡፡

## 2.2 <u>ንድፈ ሃሳባዊ መሠረት</u>

### 2.2.1 የገፀባህሪያት ምንነት

ገፀ ባህሪያት በፈጠራ ጽሑፍ ውስጥ ማለትም በረዥም ልባለድ፣ በአጭር ልቦለድ፣ በተውኔት እና በተራኪ ግጥም ውስጥ የሚገኙ የገሃዱ አለም ሰዎች አምሳያዎች ናቸው፡፡ ስለዚህም ገፀ ባህሪያት ተደራሲ ወይም አንባቢ የድርሰቱ ታሪክ የነገሌ ታሪክ አሊያም የነገሌን ይመስላል ብሎ መመለስ ያስችለዋል፡፡ በአጠቃላይ በማንኛውም ድርሰት ውስጥ ለሚተረክ ታሪክ ባለቤቶቹ ገፀ ባህሪያቱ ናቸው፡፡

እነዚህ በፈጠራ ድርሰት አለም ውስጥ የሚኖሩ ገፀ ባህርያት አምሳለ ሰብዕ ሆነው ሲቀረጹ ማንኛውንም ሰዋዊ ተግባርና እንቅስቃሴ የሚያከናውኑ ናቸው፡፡

> ‹‹ባለታሪክ፣ ገፀባህሪ ሴት፣ ወንድ ፣ሕፃን ፣ሽማግሌ፣ባልቴት በአንድ ልቦለድ ታሪክ ውስጥ የራሳቸውን ኑሮ መኖር ጠባያቸው፣ ስሜታቸው በሚመራቸው መንገድ መሄድ የሚያምኑበትን ተግባር መፈፀም እንዲችሉ ደራሲ ተጨንቆና ተጠቦ የሚፈጥራቸው የታሪኩ ድርጊት ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ አማረ /1968፣30/

ይህ ሲባል ግን ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ገፀባሕርያት የገሀዱ ዓለም ሰዎች አምሳሎች ወይም ተወካዮች በመሆናቸው ደራሲው የፈጠረላቸውን ዓለም

ዓለማቸው በማድረግ የሚንቀሳቀሱ ደራሲው ስለሕይወት ያለውን አመለካከት የሚገልጽባቸው ምናባዊ ፍጡራን እንጅ በድርሰቱ ውስጥ በተሰጣቸው ስም ወይም የመኖሪያ አድራሻ ወይም ታሪኩ በተፈፀመበት ቦታ በገሀዱ ዓለም ብንፈልጋቸው የምናገኛቸው ሰዎች አለመሆናቸው ልብ ይሏል፡፡ በሌላ በኩል Hary show ገፀ ባህሪያትን እንዲህ ሲል ይገልፃል፡፡?In literature, character has several other specific meanings, notable that of a person represnted instory,Novel,play,etc"/HarryShow1972,11/

2.2.2 የገፀባህርያት አሳሳል

አንድ ጸሐፊ የፈጠረው ታሪክ፣ ሊያስተላልፈው የፈለገው መልዕክት በትክክል ለተደራሲ ግልፅ ሆኖ ይቀርብለት ዘንድ እንደ ሌሎች የልቦለድ አላባውያን ሁሉ ለታሪኩ ተገቢ የሆኑ ገፀ ባህርያት ሊፈጥር ይገባዋል፡፡

ደራሲ ገፀባህርያትን ሲስል በአካል ከሚያውቃቸው ብዙ ሰዎች፣ ከብዙ ገጠመኙ፣ወዘተ... በመነሳት ከአንዱ አካላዊውን፣ ከሌላው ማህበራዊውን ከቀሪው ደግሞ ሥነ ልቦናዊውን ወዘተ ባህርያት ቆነጻጽሎ በመውሰድ ለድርሰት ሥራው በሚያመቸው መንገድ በመገጣጠም እንጂ እንዳለ በመገልበጥ አይደለም፡፡

> በአብዛኛው በገሀዱ አለም ያሉ ሰዎችን ለማወቅ ውጫዊ ማንነታቸውን መሠረት አድርገን ነው፡፡ ውስጣዊ ባህሪያቸውን ለማወቅ በጣም የቀረበ ግንኙነትና የብዙ ጊዜ ቆይታ ሊኖረን ይገባል፡፡በልብወለድ ዓለም ውስጥ ግን ምንም እንኳ በትንሹ ቢሆንም የሰዎችን ውስብስብ ስብዕና በቀላሉ፣ በአፋጣኝና በግልፅ ማወቅ ይቻላል፡፡/ጀምስ ፒካርኒግ1997/

አንድ ደራሲ የፈጠረውን ታሪክ በትክክል ያራምዱልኛል መልዕክቴንም በማያሻማ መንገድ ለአንባቢ ያደርሱልኛል በማለት ገፀ ባህርያትን ሲቀርጽ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል ከሚባሉት ነገሮች ዘላቂነት እና ተአማኒነት ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ዘላቂነት፡- ገፀ ባህርያት የእውኑ አለም ሰዎች ቅጅ መሆናቸውን ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ የእውኑ ዓለም ሰዎች አላቸው ብለን ከምንገምተው ባህሪያት አንዱ ደግሞ ዘላቂነት ነው፡፡ ታዲያ እነዚህ የሰው አምሳያዎች ናቸው ያልናቸው ገፀ ባህሪያት ይህን የባህሪ ዘላቂነት በተፈጠሩለት ታሪክ ውስጥ ይዘው ሊገኙ ይገባል፡፡ገፀ ባህርያት በየገፁ፣ በየንዑሳን ርዕሱና በየምዕራፉ የተለያየ ባህሪ ይዘው ብቅ የሚሉ ከሆነ ታሪኩ ዘላቂነት አይኖረውም፡፡ይህ ሲባል ግን በጭራሽ ለውጥ አይኖራቸውም ማለት አይደለም፡፡

ለውጣቸው ግን በአሣማኝና በበቂ ምክንያት መደገፍ መቻል አለበት ከሚል እሳቤ የተነሳ ነው፡፡

አንድ ገፀባህሪ ለገባበት ሁነት፣ ለፈፀመው ድርጊት ወይም ለሚሰጠው ምላሽ አንባቢ እኔም ሆንኩ ሌላ ሰው በእርሱ ቦታ ብንሆን ልናደርገው የምንችለው ጉዳይ ነው ብሎ አምኖ እንዲቀበለው ሊያደርግ የሚችል ምክንያት ደራሲው ሊሰጥ ይገባዋል፡፡

> የእውኑ አለም ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው በየደረጃው በሚያጋጥሙአቸው የተለያዩ ሁኔታዎች ለምሳሌ በእድሜ መብሰል፣በትምህርት፣...በሕይወታቸው አቅጣጫ ለውጦች ሊገጥሟቸው ይችላሉ፡፡....ነገር ግን ያለበቂ ምክንያት የሚከሰቱ አይደሉም፡፡... ዋናው ቁም ነገር ለመጣው የባህሪም ሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ ከታሪኩ ጋር የተቆራኘ አሳማኝ ምክንያት መገኘቱ ነው፡፡ /ዘሪሁን 1998 ÷162-163/

ተዓማኒነት ገፀባህርያቱ ዘላቂ፣ ኢፍፁምና ግለወጥ ሆነው መቀረፃቸው በሌላ መልኩ ተዓማኒነታቸውን ይነግረናል፡፡ ገፀባህርያት የየራሣቸው የሆነ ግብ ያላቸው ድርጊታቸውና አስተሣሰባቸው ከማንነታቸው የሚመነጭ የጊዜያቸውና የአካባቢያቸው ወኪሎች ናቸው፡፡ አንባቢው የምናቡ ዓለም የእውኑ ዓለም ሰዎችን ባህሪያት የተጐናፀፉ ናቸው ብሎ እንዲቀበላቸው ሶስቱንም በጥምረት ማለትም ዘላቂነት፣ ኢፍፁምና ግለለወጥን ማካተት አለባቸው፡፡ ይህም ለታሪኩ ተዓማኒነትን ያጎናጽፈዋል፡፡

ለአንባቢ የገፀባህሪያት ሀዘናቸው ሀዘኑ፣ ችግራቸው ችግሩ ደስታቸው ደስታው ወዘተ . . . የሚሆነው ደራሲው በተዓማኒነት የሣላቸው ገፀባህሪያት ባህሪይ ውጤት ነው ደራሲው ለሚፅፍበት ማህበረሰብ ጋር በሃሳብ እና በገቢር የሚስማማው እንዲሁም ለገቡበት የፈጠራ አውድ ተዓማኒ የሆነ ድርጊት የሚፈፅሙ ገፀባህሪዎችን ማቅረብ አለበት፡፡

### 2.2.3 የገፀባህርያት አሳሳል ደረጃዎች

አንድ ፀሐፊ ተውኔት ወይም ደራሲ፣ በድርሰቱ ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ወይም ለማሳየት የፈለገውን ህይወት፣ ከፈጠራቸው ገፀ-ባህርያት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡የተፈጠሩት ገፀ- ባህርያት በድርሰቱ ለማስተላለፍ የተፈለገውን አቢይ ቁምነገር ማስጨበጥ፣ ለማሳየት የተፈለገውን ህይወት ማሳየት መቻል አለባቸው፡፡ ይህም ማለት ገፀ-ባህርያቱ በታዳሚ አይነ ህሊና ውስጥ መስረጽ የሚችሉት እንደገሃዱ ዓለም ሰዎች ሲንቀሳቀሱ፣ ሲያስቡ፣ ሲናገሩ፣ ሲያዳምጡ፣ወዘተ... ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ ድርሰት ውስጥ ገፀ-ባህርያት የገሃዱ ዓለም ሰዎችን መልክና ግብር ይዘው ለተደራሲ ምናብ በተለያየ መንገድ የመሳሉ ወይም የመቅረፁ ዘዴ የገፀ-ባህርያት አሳሰል ወይም

አቀራረፅ በመባል ይታወቃል፡፡ ገፀ-ባህርያት በዚህ ዘዴ ተስለው ካልቀረቡ ተደራሲ አንዳቸውን ከአንዳቸው ለይቶ በቅጡ ሊያውቃቸው አይችልም፡፡ ገፀ-ባህርያት በአግባቡ ካልተሳሉም ለተደራሲ ምናብ ቀረቤታ አይኖራቸውም፡፡

> The creation of images of imaginary persons in drems, narrativ poetry, the novel, and the short story is called characterization. In effective narrative literature,fictional persons., through characterization, become so credible that they exist for the reader as real people.Without characterization, no thesis, no plot, and no setting can develop genuine interest for a reader or cause him to care what happens, or does not happen, to whom and why, Harry show (1992;71)

በመሆኑም አንድ ፀሐፊ- ድርሰቱ በተደራሲያን ዘንድ ተቀባይነትን ያገኝ ዘንድ ለሚፈጥራቸው ገፀባህርያት አሳሳል /አቀራረፅ/ ትልቅ ግምትና ትኩረት መስጠት አለበት፡፡ፋንታሁን እንግዳ <u>**ዝክረ-ተውኔት**</u> በተባለው መፅሐፍ "ሀብርት ሀፊነር" የተባለውን ሰው በመጥቀስ የገፀ-ባህርያት አሳሳል አራት ደረጃዎች ያሉት መሆኑን በመግለጽ ለታዳሚ እይታና ልቦና ቶሎ በሚጨበጡበት ቅደም ተከተል አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ እና ሞራላዊ የአሳሳል ደረጃዎች እንደሆኑ ጽፏል፡፡ በእነዚህ የገፀ-ባህርያት የአሳሳል ደረጃዎች በአንድ ድርሰት ውስጥ ያሉ ገፀ- ባህርያት ሁለንተናዊ መልክ ጥርት ባለ መንገድ በመቅረቡ፣ የገፀ-ባህርያትን አካላዊ አቋም፣ አመል፣ ታሪክ፣ አብሮ የመኖርና የመገለል ፀባይ፣ የውስጣዊ አስተሳሰባቸውን፣ ውጪያዊ ድርጊታቸው፣ በድምሩ እነሱነታቸውን የሚገልጽ ሁሉን አካል እንቅስቃሴያቸው ፍንትው ባለ መንገድ ያቀርባል፡፡

በመሆኑም እነዚህ አራቱ የገፀባህሪያ አሣሣል ደረጃዎች ደግሞ ጠቅለል ተደርገው ሲታዩ ለሁለት ይከፍላሉ፡፡ እነርሱም አካላዊ ገፅታና ህሊናዊ ገፅታ በመባል ይታወቃሉ፡፡ አካላዊ ገፅታ አካላዊውን ወይም የውጭውና አፋዊውን ሲይዝ ውስጣዊ ወይም ህሊናዊ ገፅታ ደግሞ ማህበራዊ፣ ሥነ ልቦናዊና ሞራላዊ አሣሣሎችን ይጠቀልላል፡፡ ውስጣዊ ሲባል ውስጣዊ ስብዕናን የምናይበት አሣሣል ነው፡፡ ስለሆነም የገፀባህሪያቱን አሣሣል ደረጃዎች ለሁለት ከፍለን እናያቸዋለን፡፡

2.2.3.1 ውጫዊ ገፅታ

የአንድን ሰው አካላዊ አቋም ዓይተን "እንዲህ ነው" እንደምንለው ሁሉ ገፀባህሪያትም የሚለዩበት ውጫዊ ወይም አካላዊ ወይም አፋዊ መልክ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የተለያዩ ምሁራን ስለ ውጫዊ ገፅታ ምንንት ተመሣሣይ ሃሣብ ይሰጣሉ "ገፀባህሪይ ምን እንደሚመስል ቀይ ይሁን ጥቁር ፣ረጅም ፣ወፍራም ይሁን ቀጭን ወይም ድምፅ ጉርናና ይሁን ድምፀ ሠላላ መገለፅ አለበት፡፡"/ዘሪሁን 1983፣32/ በማለት የሰውነቱን አቋም የገፁን ቀለምና የድምፁን ውፍረትና ቅጥነት ማካተት እንዳለበት አብራርቷል፡፡ በተጨማሪም ፋንታሁን /1994፣23/ በበኩሉ "የገፀባህሪያት አካላዊ አቋም ሲባል. . . የገፃባህሪውን ፆታ ፣ እድሜ ፣ የሰውነት መጠንና ቀለም ወይም መልክ የሚመለከት ነው፡፡"ይላል ከዚህም ሌላ በአለባበስ፣ በአነጋገር፣ በአረማመድ እንዲሁም በስም ስንለያቸው እንችላለን፡፡

2.2.3.2 ውስጣዊ ገፅታ

ውስጣዊ ገፅታ የምንላቸው ማህበራዊ፣ሥነልቦናዊንና ሞራላዊውን አጣምሮ በመያዝ የሰው አመለካከት፣ አስተሣሰብ፣ እምነትና ፍልስፍናን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ በዚህም ዙሪያ የተለያየ ሙሁራን ስለ ሂሊናዊ ወይም ውስጣዊ ገፅታዎች ምንነት ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ ፋንታሁን /1994፣23/ "ማህበራዊ ኑሮው ደግሞ የምጣኔ ሐበት ሁኔታውን፣ የሙያ መስኩን፣ ትምህርታዊ ዳራውንና ቤተሰባዊ ግንኙነቱን ሁሉ አካቶ ይይዛል፡፡" ማህበራዊ ኑሮውን ብቻ ሣይሆን የራሱን ሰብእናዎች በጣም ደግ፣ ሩህሩህ ወይም ጨካኝ ወዘተ. . . እየተባለ በዝርዝር ስለባህሪው/ዋ/ ስለአስተሣሰቡ/ዋ/ የሚነገሩት ሁሉ ይካተታሉ /ዘሪሁን፣1992/፡፡ የሰው ልጆችን የተደበቁ ረቂት ባህሪያትንና ስሜቶችን በልቦለዶች ውስጥ በግልፅ የምናያቸው በገፀባህሪያት ውስጣዊ ገፅታዎች አማካኝነት ነው፡፡

እነዚህ ሁለት ገፅታዎች የአንድን ልቦለድ ገፀባህሪያት ምንነትና ልዩነት ለመረዳት አስፈላጊነታቸው የላቀ ነው፡፡ የገፅታዎቹ አቀራረብና አገላለፅ እንደ ደራሲያኑ ዓተያይ እንጂ በማንኛውም ልቦለድ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ገፀባህሪያትም በእውኑ ዓለም የምናውቃቸው ሰዎች መስለው በአንባብያን አእምሮ የሚቀረፁት በእነዚሁ የገፀባህሪያት ገጽታዎች ጥምረት ነው፡፡

2.2.4 የገፀባህርያት አቀራረብ ዘዴዎች

አንድ ደራሲ በሚጽፈው ታሪክ ውስጥ አመቺ ነው ብሎ የፈጠረው አውድ በፈቀደለት መንገድ ገፀ ባህርያትን ቀርጾ ወይም ስሎ ለተደራስያን የሚያስተዋውቅባቸው መንገዶች ርቱዕ እና ኢርቱዕ ወይም ተውኔታዊ የአቀራረብ ዘዴዎች ናቸው፡፡

ርዕቱ የአቀራረብ ዘዴ የሚባለው ተራኪው ወይም ደራሲው ስለሳላቸው ገፀ ባህሪያት፣ አለያም ከዳር ቁሞ የሚታዘብ ሌላ ገፀ ባህሪ በድርሰቱ ውስጥ ስላሉ መሰሎቹ ገፀ ባህርያት ምንነትና ማንነት ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የሚያሳውቅበት ዘዴ ነው፡፡በዚህ የአቀራረብ ዘዴ በአብዛኛው የገፀ ባህርያት አካላዊና ህሊናዊ መልክ በቀጥታ ይገለፃል፡፡

ኢርቱዕ የገፀባህርያት አቀራረጽ ዘዴ ግን ደራሲው ወይም ተራኪው ስለ ገፀ ባህርያት እገሌ እንዲህ ነው፣ እገሊት እንዲህ ነች በማለት የሚያስተዋውቅበት ሳይሆን ገፀ ባህርያትን በተዘዋዋሪ መንገድ በመግለጽና እራሳቸውን በምልልስ እያናገረ እና በድርጊታቸው እንዲታዩ እያደረገ አንባቢ ማንነታቸውን እንዲረዳ የሚያደርግበት የገፀ ባህርያት አቀራረብ ዘዴ ነው፡፡

### 2.2.5 የገፀባህርያት አይነቶች

በልቦለድ ታሪክ ውስጥ የሚሳሉ ገፀ ባህርያት ህልውና ለታሪኩ አንዳች ፋይዳ ሊኖረው ይገባል፡፡ ለልቦለዱ የገፀ ባህርያት አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት በዝተው የልቦለዱን ታሪክ መያዣ መጨበጫ እንዳያሳጡት፤ አንሰውም ጎደሎ እንዳያደርጉት በተገቢው የቁጥር መጠን መቅረብ አለባቸው፡፡ ለታሪኩ ፍሰት ምሰሶና ማገር ሆነው መዋቅሩን የሚገነቡ፣ ለታሪኩ ህያውነት ዋና የሆኑ ገፀ ባህርያት የመኖራቸውን ያህል ድርሻቸው አናሳ የሆነ ገፀ ባህርያትም ይኖራሉ፡፡

የልቦለድ ገፀ ባህርያት በድርሰት ውስጥ በሚኖራቸው ባህሪ /ስብዕና/፣ የቆይታ ጊዜ፣ በአንባቢ ሊፈጥሩ በሚችሉት ጥያቄ ወዘተ… አቢይና ንዑስ ወይም ፈርጀ ብዙና ፈርጃንድ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

በአንድ ድርሰት ውስጥ በብዙ ቦታዎች የሚታዩ፣ አብዛኛው ታሪክ የነሱ የሆነና በብዙ ሁነት ውስጥ ለረዥም ጊዜ የሚታዩ ገፀ ባህርያት ፈርጀ ብዙ የሚባሉት አይነት ሲሆኑ፤ በተቃራኒው ደግሞ ብዙ ውስብስብነት የማይታይባቸው፣ በአንባቢ ዘንድ ተለይተው የሚታወቁበት አንድ አመል ያላቸው እና በተደጋጋሚ አንድ ነጠላ ጉዳይ ብቻ የሚያሳዩ ታሪካቸው ብዙም ዕድገት ሳያሳይ የሚቆመው ደግሞ ፈርጃንድ ገፀ ባህርያት የሚባሉት ናቸው፡፡

## 3 የገፀባህሪ አሳሳል "በጠፍ ከዋክብት" ረዥም ልቦለድ

### 3.1 የጠፍ ከዋክብት ታሪክ ባጭሩ

ጄነራል ፍራንኮ አገሩ ሮም የጣለችበትን ግዳጅ ለመወጣት ሸዋ ክፍለ ሀገር ልዩ ስሙ ጁሩ የሚባል አገር ተገኝቷል፡፡ እዛም አቶ በሼ የሚባሉ ለሮማ መንግስት አገልጋይ የሚመስሉ ነገር ግን ለአገራቸው አርበኞች መረጃ የሚሰጡ ሰው ቤት ጄነራሉ ይመላለሳል፡፡ በዚህ አጋጣሚም የአቶ በሼ ሴት ልጅ ሴማዊትን ያፈቅራል በፍቅሯም አቅሉን እንደሣተ ፍቅር ምንድ ነው? ጥላቻስ? የሚል ጥያቄ በማንሣት ታሪኩን ይጀምራል፡፡

የአቶ በሼ ቤት የሮም ወታደር ኃላፊ የሆነውን ጄነራል ፍራንኮ እና በዱር በገደል ለኢትዮጵያ ነፃነት የሚዋጉትን አርበኞች ያስተናግዳል፡፡ የሮም ወታደሮችን በግልጽ፤ አርበኞችን በሚስጢር ለራስ ብቻ በሚገባ ልዩ ሚስጢራዊ መልዕክት ተበታትነው ያሉትን አርበኞች መልዕክት በመቀበል፡፡የተቀበሉትን ለሌላኛው በማስተላለፍ  እንዲሁም ቀለብ፣ የመሣሪያ አቅርቦት፣ ከሮም ወታደር የሰሙትን ሚስጢር ለአርበኞቹ በመላክ አገራዊ ግዴታቸውን የሚወጡ ሰው ናቸው፡፡ ነገር ግን ሁለት መልክ ያላቸው ብልህና አስተዋይ አርበኛ ሲሆኑ ሴማዊትም የአባቷን ዱካ በመከተል የድርሻዋን የምትወጣ ውብ ጠይም ወጣት ሴት ናት፡፡

ጄነራል ፍራንኮ እና ምክትሉ ሲልቪዮ በቀላሉ አገሪቱን ለመቆጣጠር የሚቻልበትን መንገድ ቀና ለማድረግ የአገራቸውን ግዳጅ ለመወጣት ቢመጡም አንድ ቀን እንኳ በሃሣብ ተግባብተው የማያውቁ አዛዥና ታዛዥ ናቸው፡፡ ምክትሉ ለሮማ መንግስት እውነተኛ ወዳጅ ናቸው የሚላቸው ኪዳኔና ፊታውራሪ መነሻ የሚባሉት ሰዎች ብቻ ናቸው ሲል በአንፃሩ አቶ በሼን የሚጠራጠር ሰው ነው፡፡ ጄነራል ፍራንኮ ግን አቶ በሼና ቤተሰቦቻቸውን እውነተኛ የሮም ወዳጅ እንደሆኑ ይመሠክርላቸዋል በዚህም የተነሣ ምክትሉ ምንም ማድረግ ባለመቻሉ አቶ በሼን እንደተጠራጠረ  ብሎም የአለቃው መታወር እያሣዘነው ግራ ሲጋባ ይስተዋላል፡፡

ተፈሪ ግርማ ሞገሱ የሚያስፈራ ወጣት ሲሆን ለአገሩና ለወገኑ ፍቅር ሲል "ወንዶች በረሃ" የሚባል ጫካ  ውስጥ ገብቶ የሚዋጋና  የሚያዋጋ አርበኛ ነው፡፡ ተፈሪ የአቶ በሼ እህት ልጅ ሲሆን  አስፈላጊውን መረጃ፣ ቀለብና ቁሣቁስ በአቶ በሼ በኩል ስለሚደርሰው ለሮም ወታደር የጉን ውጋት ለመሆን በቅቷል፡፡ ይህንንም ኪዳኔ የተባለው  የሮማ ባንዳ አቶ በሼ ከሮማ መኮንኖች መረጃ ለተፈሪ እንደሚሰጡ ለማጋለጥ ያደረገው ጥረት  በአቶ በሼ ጥበባዊ መልስ እንዲሁም በሴማዊት ብልሃት ሊከሽፍበት ቢችልም አቶ ኪዳኔና ፊታውራሪ መነሻ የተባሉት ባንዳዎች የሴማዊትን ባል የተፈሪ

የቅርብ ወዳጅ የሆነውን ሠርቀኃይልን ትነግሣለህ በሚል ሀሰተኛ ትንቢት በአንድ ቄስ በኩል በማስነገር ተፈሪን አስከድተው ለማስገደል ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ተፈሪ ጣልያንን ለማስወጣት በሚደረገው ማንኛውም ትግል ላይ ተሣትፎ የሚያደርግ ወጣት አርበኛ መሆኑን የተገነዘበው ቅጣው የተባለ አርበኛ፣ እንደ ተፈሪ አገራቸውን ነፃ ለማውጣት በዱር በገደል ያሉ አንቱ የተባሉትን የጐጃምና የሸዋ የጦር ሰዎች በቅንጅት ጠላትን ለማጥቃት ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለመወያየት መራቤቴ በተባለ አገር በተሰበሰቡበት ወቅት፣ የተፈሪ የቅርብ እረዳት የሆነው ሰረቀኃይል አጠገቡ አልነበረም፡፡ በውይይታቸው ወቅት አጀንዳቸው ጠላትን እንዴት ማጥቃት እንዳለባቸው ለመነጋገር ቢሆንም በንጉሱ ጉዳይ ጭቅጭቅ መፍጠራቸውና አለመግባባታቸው ጐልቶ የታየበት ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የሰበሰባቸው ቅጣው የተባለ አርበኛ ሰረቀኃይልን ጫካ ውስጥ ይመለከተዋል፡፡ ወዲያውኑም ለተሰብሣቢ ጓደኞቹ ቦታ እንዲለወጡ ያደረግና ከጥቃት ያመልጣሉ፤በዚህ ሁኔታም ይለያያሉ፡፡

ተፈሪ ሰረቀኃይል ከባንዶች ወገን እንደሆነና እንደከዳው ብሎም ሊያጠፋው እንደሆነ ከአጐቱ ልጅ ከሴማዊት ይሰማል፡፡ ሰረቀኃይል የሴማዊት ባል ሲሆን ጫካ የገባውም በሚስቱ ገፋፊነት እና ባልገዛም ባይነት ነው፡፡ሠረቀኃይል ከተፈሪ ዋነኛ ተዋጊዎች መሀል አንዱ ነው፡፡ ሆኖም ግን ሴማዊት ሠረቀኃይል እንደከዳ መረጃውን ከጣሊያኑ ጄነራል እንዳገኘች በማያወላውል መልኩ ለተፈሪ አስረዳቸው፡፡ ተፈሪም ለስብሰባ መራቤቴ በሄደበት ወቅት እንዲከተለው ነግሮት ነበር፡፡ነገር ግን ሰረቀኃይል እንዳልተከተለው ብሎም ጥቃት እንደተሰነዘረም አስታውሶ ስብሳባ እንደነበር ለጣሊያኖች የተናገረውና ሊያስጨርሣቸውም የነበረው ሠረቀኃይል መሆኑን ተረዳ፡፡ ተፈሪ በዚህም በጣም አዘነ ከዚያም መዝሙረ ዳዊት አወጥቶ ማንበብ ጀመረ፡፡ ሴማዊትም እርሷ እንድትገለው የሶስት ቀን እድሜ እንዲሰጣት ትለምነውና ይለያያሉ፡፡

ሴማዊትም ተፈሪን እንዲከዳው አሣምነዋለሁ በሚል ሰበብ በጄነራል ፍራንኮ አማካይነት ከሠረቀኃይል ጋር የሚገናኝበትን ስፍራ ታመቻችና ሠረቀይልን ታገኘዋለች፡፡ እንዳገኘችውም መሣሪያ ጭንቅላቱ ላይ በማነጣጠር አንተ ባንዳ ወድሜን ከዳህው፣ኢትዮጵያን ከዳህት እና ለጠላት አጎበደድክ፣ ፍቅሬንም ረገጥክ፣ ቃልኪዳንህንም በጭቃ ለውሰህ ቀበርከው በማለት እየተሳደበች እያለ ከርቀት ምክትል ጄነራል ሲልቪዬ ሠረቀኃይል ላይ መሣሪያ እንዳነጣጠረች ያስተውላል በዚህ ቅፅበት ሠረቀኃይልን ተኩሣ ትገለዋለች ወዲያው ምክትል ጄነራል ሴማዊት ላይ ይተኩሳል እርሷም ዞራ ትተኩሣለች፡፡ በዚህ ሁኔታ ተከትለዋት የነበሩት ጄሌዎቿ፣ምክትል ጄነራሉና ተከታዬቹ ላይ ተኩስ ይከፍታሉ በዚህም ሣቢያ በአካባቢው ጦርነት ይቀሰቅሳል፡፡ ሴማዊትም፣

የተከተሏትም ሰዎች፣ ምክትል ጄነራሉም ይሞታሉ፡፡ አካባቢው ላይ ተፈሪ መጥቶ ጦርነቱ ይፋፋማል፡፡

በመጨረሻም አርበኞቹ ድል ያደረጉና የጣሊያን ሠራዊት ከአገሪቱ ጥርግርግ ብሎ ሲወጣ ጄነራል ፍራንኮም በምርኮ ወደ አገሩ ይገባል፡፡ ንጉሱም ከተሰደዱበት አገር ወደ አገራቸው ይመለሳሉ፡፡ ተፈሪም በጦርነቱ ወቅት ሞተ ተብሎ በመወራቱ የጣሊያን ወታደሮችም ሞተ ብለው አስበው ነበር፡፡ ሞተ ብለው ያስወሩት ግን አጎቱ አቶ በሼ በመቁሰሉ ምክንያት በደንብ  እንዲያገግም የጣሊያን ወታደሮች አስሰው እንዳያገኙት ያደረጉት ዘዴ ነበር፡፡ በቆሰለ በሰባተኛ ወሩ አገሪቱ ነፃ ወጣች ተባለ፡፡ እርሱም አገሬ ነፃ ወጣች ብሎ አጐትህ አስጠርተውሀል ሲባል ከነበረበት ወደ አጐቱ ቤት በፈረሱ እየጋለበ ሲሄድ ወታደሮች ከበው እጅ ስጥ ይሉታል እርሱ ግን ምን እጠፋሁና ይላል፡፡ በዚህም ምክንያት ጦርነት ውስጥ ይገባል ለአገሬ በተዋጋሁ ለነፃነቷ በቆሰልኩ እንዴት እጅ ስጥና ይቅርታ ጠይቅ እባላለሁ፡፡ በማለት በነገሮች በማዘን መልሶ ጦርነት ውስጥ ይገባል፡፡ ጥይት መጨረሱን ሲረዳ ፈረሱ  ላይ እንዳለ ፊቱን ወደ ገደል አዙሮ የቀሩትን ሁለት ጥይቶች አንድ ለፈረሱ አንድ ለራሱ በመተኮስ ፈረሱንም እራሱንም ያጠፋል፡፡

ባንዳ የነበሩት ኪዳኔና ጄሌዎቹ ጣሊያን ሲወጣ የውስጥ አርበኛ በመባል ራስ ተብለው ተሾሙ አቶ በሼ ለሹመት ቢጠሩም ወደ አዲስ አበባ ሣይሄዱ ቀሩ፡፡ ከጦርነቱ በፊት ጠፍቶ የነበረው የተፈሪ ወንድም አየለ ወደ አገሩ ሲመለስ የሆነውን ሁሉ ሰማ፡፡ በመጨረሻም አቶ በሼና አየለ የኢትዮጵያንና የተፈሪን ጠላቶች ለመግደል ይወጥናሉ፡፡ አቶ በሼ ራስ ኪዳኔን የተፈሪ ወንድም አየለ ደግሞ አራት ያህል ጄሌዎቹን የሹመት ልብሣቸውን አስወልቀው በመግደል የሹመት ልብሣቸውንም የአቶ በሼ ውሻዎች የተቀበሩበት ቦታ ላይ ያቃጥላሉ፡፡

በመጨረሻም ጥቂት የተፈሪ ጓደኞች በወታደር ተከቦ እራሱን መግደሉን ሲሰሙ የሹመት  ልብሳቸውን አውጥተው በማቃጠል  ሹመታቸውን በራሣቸው ፈቃድ ሲጥሉ፣ ጥቂት ጓደኖቹ በተፈሪ ሁኔታ በማዘን እራሣቸውን ወደ ገደል በመወርወር ያጠፋሉ፡፡ ባንዳዎቹ በነፃይቱ ኢትዮጵያ ሊታመን በማይችል መልኩ የበላይነት ተጐናፅፈዋል በማለት ታሪኩ ይጠናቀቃል፡፡

### 3.2 የዋና ገፀባህሪ አሳሳል

#### 3.2.1 አካላዊ ገለፃ

ደራሲያን በልቦለዶቻቸው ውስጥ ገፀባህርያትን በልዩ ልዩ አሣሣል ሊስሉ ይችላሉ፡፡ በተለይ የልቦለዱ ዋና ዋና ገፀባህርያትን አጉልቶ ለማሣየት እንዳንድ ደራሲያን ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካከል የገፀባህርያቱን አካላዊ ማንነት በደራሲው፣ በዋና

ገፀባህሪው፣ በተራኪው ወይም በንዑሣን ገፀባህሪያት አማካይነት እንዲገለጹ ያደርጋሉ፡፡ አካላዊ ገለፃ በዋናነት አፋዊ መልክ መዘርዘር፣ በስም ማስተዋወቅና አልባሳት በመግለፅ የሚካተቱበት ሲሆኑ ተደራሲው በቀላሉ የዋና ገፀባህርይውን አፋዊ ማንነት እንዲለይ ያደርገዋል /ዘሪሁን፣1992፣68/ በዚሁ መሠረት የየጠፍ ከዋክብት ውስጥ ሴማዊት፣ ጄነራል ፍራንኮ፣ ምክትል ጄነራል ሲልቪዮ፣አቶ በሼ፣ተፈሪና ኪዳኔ አካላዊ መልክ ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡

3.2.1.1 የሴማዊት አካላዊ አሳሳል

ነጩ ጀግና ጄነራል ፍራንኮ ከሴማዊት ፍቅር የጀመረው አገሩ የጣለችበትን ግዳጅ ለመወጣት ጁሩ የሚባል አገር በተገኘበት ወቅት ነው፡፡ ሴማዊትን ያያት አባቷን አቶ በሼን ለማማከር ወደ ቤታቸው በሚመላለሰው ወቅት ነው፡፡ ጀነራሉ በፍቅሯ እንዲህ ሊወድቅ የቻለው ባላት አካላዊ መልክ ሲሆን አካላዊ ማንነቷንም ደራሲው እንዲህ ሲል ይገልፃታል፡፡‹‹. . . ጠይሙና_መስህባዊ ፊቷ ከተስተካከለ እንዝርት አቋሟ ጋር . . .፡፡/ የጠፍ ከዋክብት፣1/፡፡ በማለት ታሪኩ ይጀመራል፡፡ በዚህም ብቻ ሳይቆም በታሪኩ ሂደት አካላዊ መልኳ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> ‹‹ . . . የተዋበ የሀበሻ ቀሚስ ለብሣ፣ ኩታ ደርባለች ፀጉሯም ውብ አድርጋ ተሰርታለች፡፡ አለባበሷን ሲያስተውል "በአውሮፓ እንኳን እንዲህ ዓይነት ውብ አለባበስ አላየሁም" ሲል ተደነቀ ፡፡ እንዲህ ተውባና አምራ ሲመለከታት…፡፡/ የጠፍ ከዋክብት ፣157/
>
> ". . . ከንፈሯ ስስ ነው፡፡ ቆዳዋ ስስ ነው፡፡ ፀጉሯ የሀር ነዶ ይመስላል አፍንጫዋ ስልክክ ያለ ነው፡፡ አይኗ አጥቢያ ኮከብ ነው፡፡ ስስ የፊቷ ቆዳ ጥቁር አይደለም፣ ቀይም አይደለም፣ ነጭም አይደለም፣ ልዩ ነው፡፡ ልዩ ቀለም ነው ፡፡"/የጠፍ ከዋክብት ፣162/

የሴማዊት አካላዊ ገለፃ በጄነራል ፍራንኮ ብቻ ተገልጾ አላቆመም፡፡ አባቷ አቶ በሼና ዘመዶቿ በግራ እጇ እንዳትጠቀም ሲገስጿት ይስተዋላል፡፡ ደራሲውም እንዲህ ይገልፃታል‹‹…አባቷ ደረት ላይ ሆና አባቷን እያሻሸች ትፍለቀለቃለች፡፡ ሆኖም ከተመከረች በኂላ እንኳ ፀጉራቸውን የምታሻሻቸው በግራ እጇ መሆኑን እያስተዋሉ …››፡፡/የጠፍ ከዋክብት፣186/ በመሆኑም ለሥራም ለጨዋታም ብቻ ማንኛውንም ነገር ለማከናወን ግራ እጇ እንደሚቀድም ለመረዳት ይቻላል፡፡ ደራሲውም ይህንን ሀሣብ እንዲህ ያጠናክረዋል፡፡‹‹…እሷም እንደ ተፈሪ ሁሉ ግራኝ ነች ግራኝነቷን የወረሰችው ከቤተሰቧ ይሆን ወይ ከተፈሪ አታቅም ስትናደድ እንደ ተፈሪ ሁሉ ግራ እጇን

ታወናጭፋለች...››፡፡/የጠፍ ከዋክብት 185/የሴማዊት አካላዊ ገለፃ በጄነራል ፍራንኮና በአቶ በሼ እንዲሁም በዘመዶቿ ብቻ አያበቃም ይህንንም ደራሲው ተፅሐፊ የተባለ ንዑስ ገፀባህሪይ እንዲህ ሲገልፃት ያስነብበናል..... በለበሰችው ጥበብ ተውባና ወገቧን ይዛ ተፅሐፊ ሲያስተውላት እንዴት ሀያልና በራሷ አጥብቃ የምትተማመን ንግስት መስላ ታየችው. . ፡፡ /የጠፍ ከዋክብት፣ 188/ ከዚህ የምንረዳው ውበቷ መልኳ ብቻ ሣይሆን የአመለካከት አቋሟ ጭምር መሆንን ልብ ይላል፡፡

ይህ አይነቱ የገፀባህርይ አካላዊ ገለፃ ርቱዕ አቀራረብ ከሚባለው ዘዴ እንዱ ነው፡፡ ይህም አንባቢ ገፀባህርይውን ሰው ነው ብሎ እንዲቀበል ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን በክለሣ ድርሣኑ ላይ ተጠቅሷል፡፡ በዚህ ፅንሰ ሃሣብ መሠረት ስለ ሴማዊት የተሰጠው ገለፃ፡፡ ሴማዊትን በስም ብቻ ሣይሆን በመልኳና በተክለ ሰውነቷ ልንለያት እንድንችልና ምስል እንድንፈጥርላት አድርጓል፡፡

በመሆኑም በሴማዊት አካላዊ ገለፃ መሠረት አንባቢው በገሀዱ አለም ከሚያውቃቸው የገጠሪቷ ኢትዮጵያ ሴቶች መርጦ ሴማዊት ይች ትሆን ሊል ያስችለዋል፡፡ ምክንያቱም የቀረበው ገለፃ በታሪኩ ውስጥ አንድ ቦታ ላይ ብቻ ሣይሆን በታሪኩ የተለያየ ቦታ በመጠቀም ምስል ከሣች አድርጐታልና፡፡

3.2.1.2 የጄነራል ፍራንኮና የምክትል ጄነራል ሲልቪዬ አካላዊ አሣሣል

ደራሲው የጄነራል ፍራንኮንና የምክትል ጄነራል ሲልቪዬን ቁንጹል በሆነ አካላዊ ገለፃ አስቀምጧቸዋል፡፡ እነዚህ ሁለት የማይዋደዱ አዛዥና ታዛዥ የጦር መኮንኖች በተራኪው አንደበት በታሪክ ሂደት ውስጥ በተለያየ ቦታ ተገኝተው እናያለን፡፡ ነገር ግን አካላዊ ገለፃቸው ውስን በሆነ መልኩ  አንድ ቦታ ላይ ብቻ በጥምረት አስቀምጦታል ይህም እንዲህ ይነበባል፡፡

> ‹‹ፁጉራቸው በሽጋ ሁኔታ የተበጠረ፣ግሩም ወታደራዊ አለባበስ የለበሱ፣ እጅግ የሚማርክ አቋም ያላቸው ሁለት አውሮፓውያን ቆመው ይወያይሉ፡፡ ፁጉራቸው ንፋስ ብትን ብትንትን ያደርገውና መልሶ ደግሞ ዘንፈልፈል ያደርገዋል ከሩቅ ለሚመለከታቸው የእግዜር መልዕክተኛ፣ የመላዕክት ዝርያ ይመስላሉ፡፡ ውበታቸው፣ ግርማቸው፣ ቆራጥነታቸው እና አጠቃላይ ሁኔታቸው ያሉበት አካባቢን ውበት ፀዳል አብርቶታል...፡፡››/የጠፍ ከዋክብት ፣7/

ከዚህ እንደምንረዳው ደራሲው የተጠቀመው አካላዊ ገለፃ የሁለቱን አውሮፓውያን ወታደሮች መልክ፣አቋምና አለባበስ ለመግለፅ ሞክሯል፡፡ ይህም

ሴማዊትን ከተገለፀችበት አካላዊ ገለፃ ዝቅያለ በመሆኑ የታሪኩን አጓጊነት ቁጥብ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በተለይ ጄነራል ፍራንኮ ከምክትል ጄነራል ሲልቪዮ ተነጥሎ ቢገለፅ ኖሮ የተሻለ ይሆን ነበር ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሁለቱም አውሮፓዊ አካላዊ ገለፃ አንድ አይነት ተደርጐ መሣሉ የታሪኩን ፍሰት ያስተጓጉለዋል፡፡ ምክንያቱም አንዱን ከአንዱ የምንለይበት መልክ ባለመኖሩ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በአየነው አካላዊ ገለፃ መሠረት አንባቢው በገሀዱ አለም ከሚያውቃቸው አውሮፓውያን መርጦ ጄነራል ፍራንኮ ይሄ ነው ምክትል ጄነራል ሲልቪዮ ይሄ ነው ሊል አያስችለውም፡፡

### 3.2.1.3 የአቶ በሼ አካላዊ አሳሳል

በዚህ ልቦለድ ውስጥ ሌላው ዋና ገፀ ባህሪይ አቶ በሼ ናቸው፡፡ በሼ ከታሪኩ እንደምንረዳው የሴማዊት አባት የተፈሪ አጐት ናቸው፡፡ አቶ በሼ ኢትዮጵያ በጣሊያን በተወረረችበት ወቅት ለጣሊያኑ ጄነራል የቅርብ አማካሪ በመሆን ሲያገለግሉ እናያቸዋለን፡፡ ነገር ግን ከጣልያን ጄነራል የሰሙትን መረጃ ባልገዛም ባይነት ጫካ ላሉት አርበኞች መረጃ፣ የጦር መሣሪያና ስንቅ እያደራጁ ሲልኩ የሚታዩ እውነተኛና ብልሃተኛ፣ በእድሜያቸው መግፋት ምክንያት ጫካ ገብቶ አርበኛ መሆን ያልቻሉ ሆነው ከመሳላቸው በተጨማሪ ደራሲው አካላዊ አሣሣላቸውን እንዲህ ተገልጾዋል "በሼ ፈገግ አሉና ረዥም ቁመታቸውን ቀጥ አርገው አቆሙት…፡፡" /የጠፍ ከዋክብት፣23/ሲል የአካላዊ አሳሳላቸውን አንዱን ክፍል ጠቅሶ ብቻ ሣያቆም ተጨማሪ መልክ ሲሰጣቸው ይታያል፡፡ ይኸውም"አቶ በሼ አድሜያቸው በስልሣዎቹ ውስጥ ያለ ቁመታቸው ረዥም ሰውነታቸው ደልዳላ፣. . . ፡፡" /የጠፍ ከዋክብት፣24/

በታሪኩ ውስጥ አቶ በሼ ከአካላዊ ገለፃቸው ይበልጥ በህሊናዊ ገለፃቸው የማይረሱ ቢሆኑም አካላዊ ገለፃቸውም ከሎሎች ገፀባህሪያት ለይተን አቶ በሼን ለማወቅና ለተደራሲያን ቅርብ ለማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ሆኖም ግን አካላዊ ገለፃቸው እንደ ጄነራሎቹ ሁሉ ቁጥብ በመሆኑ ምክንያት ይህን ይመስላሉ ሊያስብለን አይችልም ፡፡

### 3.2.1.4 የተፈሪ አካላዊ አሳሳል

ተፈሪ ወጣት ቆራጥ፣ አስተዋይ፣ ተደርጐ የተሣለ ነው፡፡ ከአካላዊው ገለፃ ጎን ለጎን እንደ በሼ ሁሉ በህሊናው አሣሣል የማንረሳው ገፀባህርይ ቢሆንም አካላዊ ገለፃው ከሌሎች ገፀ ባህርያት ለይተን ለማወቅ ብሎም ለተደራስያን ቅርብ ለማድረግ ጠቃሚ

ነው፡፡ ሆኖም ግን ገለፃው እርግጥ በታሪኩ ፍሰት ውስጥ ጣልቃ እየገባ ቢጻፍም አካላዊው ገለፃ አንድ አይነት በመሆኑ ለታሪኩ የበለጠ ፋይዳ እንዳይኖረው አርጎታል፡፡በታሪኩ ውስጥ በተለያየ ቦታ ደራሲው እንዲህ ሲል ገልጾታል፡፡

> "የተፈሪ አጉት በሼ የተፈሪን ደብዳቤ እንብበው ሲጨርሱ ስለተፈሪ ማሰብ ጀምሩ፡፡ ተፈሪ በፈረስ ተቀምጦ፣ ፀጉሩ ወደኂላ ለቆ፣ በግራ አለንጋውን እያውለበለበ መሣሪያውን እንዳነገተ በሜዳው ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሽፍትነት የገባ ጊዜ ያሣየው ትርኢት ታስባቸው፡፡"/የጠፍ ከዋክብት፣38/39/
>
> "በአየር ውስጥ እያዩት ከሚያሽቃብጠውና ከሚያናጥረው ቀይ ፈረስ ላይ የተቀመጠውን ያን ግርማ ሞገሳም፣ ፁጉራም፣ አስፈሪ ጀግና በአንክሮ በህሊናቸው እያስተዋሉ ፈገግ አሉ" / የጠፍ ከዋክብት 39/

ከዚህ እንደምንረዳው አጎቱ በሼ በምልሰት ሆነው የተመለከቱት አካላዊ መልኩ እንድናይ አርጎ ብቻ አይቆምም፡፡ ከዚህም ባሻገር አርበኛ የትግል ጓዶቹ ስለ ተፈሪ እንዲህ ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ "በተለይ የተፈሪ ግራ እጅ ተወናጭፎ፣ዞማ ፀጉር በንፋስ ብትንትን ብሎ ወደፊት ሲወረወር ወደኂላና ወደፊት ተሽከርክሮ ሲፎክር ወደ ግራ ወደቀኝ ዞሮ ሲፎክር . . .፡፡ "/የጠፍ ከዋክብት ፣116 /በአንድ ወቅት አርበኞች ጠላትን ለማስወጣት የጥምረት እንቅስቅሴ ለማድረግ ተሰብስበው በመወያየት ላይ ሣሉ ደራሲው ወጣቱን ጀግና እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡፡

> ‹‹ ይሄ የሃያ ስምንት አመት ጎረምሣ አስተያየት ይሰጣል ተብሎ ሲጠበቅ ፀጥ ብሎ መቀመጡ የገረማቸው ሁሉ አይናቸውን ወደ ተፈሪ ወረወሩት፡፡ እዚያ ከተሰበሰቡት በእድሜ ትንሹ ተፈሪ ነው ሲሸፍት ሃያ አምስት አመቱ ነበር፡፡ አሁን ግን ሃያ ስምንት አመቱ፡፡ ግርማ ሞገሱ ግን ማንንም ማስበርገግ እና የማስደመም ኃይል አለው እንጂ የሃያ ስምንት አመት ሰው መሆኑን አይመሰክርም፡፡" /የጠፍ ከዋክብት፣ 108/

በታሪኩ ውስጥ ተፈሪ አካላዊ ገለፃ ከላይ በተዘረዘረው መልኩ ቢቀርብም በህልናዊው አሣሣል የማንረሣው ገፀባህርይም ነው በአካላዊው ገለፃም ከሌሎች ገፀባህርያት ለይተን ለማወቅና ይህን ይመስላል ብሎ ለመናገር ቢያስችለንም ገለፃው አንድ አይነት እና ድግግሞሽ በመብዛቱ አስልቺ አድርጓታል፡፡ ይህም ሲባል ስለመልኩ በመቀጠል ስለአለባበሱ ብሎም ስለአቋቋሙና ስለፈረሱ በታሪኩ ሂደት ጣልቃ እየገባ ቢጠቀሱ ኖሮ ታሪኩ ይበልጥ አጓጊና አስደሣች ይሆን ነበር፡፡

3.2.1.5 የኪዳኔ አካላዊ አሳሳል

በዚህ ልብወለድ ውስጥ ሌላው ገፀባህርይ አቶ ኪዳኔ ነው፡፡ ኪዳኔ ከታሪኩ እንደምንረዳው ለጣሊያን በባንዳነት የሚሠራና አቶ በሼን እንዲሁም ዘመዶቻቸውን ለማጥቃት በበቀልም እራሱን ለማስደሰት ብሎም ከጣሊያን መንግስት ሹመት ለማግኘት ጠንቋይ እቤቱ እስከማስቀመጥና እስከማስጠንቆል የደረሰ ሰው ነው፡፡ በመሆኑም ደራሲው ኪዳኔን የገለፀው ሲያስጠነቁል የለበሰውን ልብስ እያሳየንና በጉልበቱ ተንበርክኮ መሬት ሲስም ነው፡፡ ልብሱን ሲያሳየን እንዲህ ተፅፏል "አቶ ኪዳኔ ጥቁር ጥለት ያለውን ጋቢውን አጣፍቷል...፡፡" /የጠፍ ክዋክብት፣43/ ካለ በኂላ_ስለመንበርከኩ ደግሞ ደራሲው እንዲህ ፅፎታል፡፡ "...ትኩር ብሎ የተደፋውን ኪዳኔን አየው፡! ከዚያም " ምነው በደንብ በግንባርህ መሬቱን አልሳምከውም? ምነው በደንብ በጉልበትህ አልተንበረከክህም..."?፡፡ /የጠፍ ክዋክብት፣49/ የሚል ካልሆነ በስተቀር በተክለ ሰውነት አናውቀውም ይህ ቁጥብ ገለፃ ደግሞ ኪዳኔ በአካል ይህንን ይመስላል የሚያስብል የአቋም ገለፃ የለውም፡፡ይህ አካላዊ መልክ አለመገለፁ በምናብ የተወለደው ኪዳኔን ደግሞ ምናባዊ ስለሚያደርገው በዚህ በኩል የተደራሲውንና የገፀባህሪውን ቀረቤታ የላላ ያደርገዋል፡፡

3.2.2 ህሊናዊ አሣሣል

ገፀባህሪያት በልቦለድ ውስጥ ከሚገለፅባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ ህሊናዊ አሣሣል ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው አካላዊ መለያ እንዳለው ሁሉ በህሊናውም አንዱ ከአንዱ ይለያል፡፡ አንዱ ቆራጥ፣ ጨካኝ. . . ሲሆን ሌላው ፈሪ፣ ርህሩህ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዱ አፍቃሪ ሲሆን ሌላው ፍቅር የማይገባው ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህን ሰብዕናዎች ደግሞ እንደአላባበስ ወይም እንደ ተክለ ሰውነት በአይን አይተን የምንለያቸው ሳይሆኑ አንዱ ካንዱ በሚያደርገው ተራክቦ የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ በነዚህ ግንኙነቶች ውስጥ የተለያዩ ገፅታዎች የተላበሱ የህይወት መስመሮች ይኖራሉ፡፡ የሰዎችን አምሣል ይዘው የተቀረፁት ገፀባህርያትም የእነዚህ ገፅታዎች ባለቤት ናቸው፡፡ የገፀባህሪያቱን የትምህርት ደረጃ፣ የኢኮኖሚ ደረጃ፣ የሙያ፣ የእምነት፣ የስነ-ምግባር፣ የአስተሣሰብ ወዘተ የምናገኛቸው በዚሁ የገፀባህሪ አሣሣል ዘዴ ነው /ፋንታሁን 1990፣105 /፡፡ይህን ዘዴ መሠረት አድርገን በየጠፍ ከዋክብት ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ገፀባህርያት ውስጣዊ ማንነት እንፈትሻለን፡፡

3.2.2.1 የሴማዊት ህሊናዊ አሣሣል

ሴማዊት በልቦለድ ውስጥ ታሪኩ ወደፊት እንዲጓዝ ዋና ተጠቃሽ ከሆኑት ገፀባህራያት መካከል አንዷ በመሆኗ ህሊናዊ አሣሣሏን እንደሚከተለው እንመረምራለን፡፡ሴማዊ ት እንደ አባቷ በሼ ሁሉ ለአገርና ለወገና ክብር በዱር በገደል ላሉ አርበኞች ከአባቷ ጋር በመሆን የድርሻዋን የምትወጣ ወጣት፣ ቆንጆ፣ ብልህ፣ ቆራጥ፣ ጀግና ሴት ሆና የተሣለች ገፀባህሪይ ናት ከታሪኩ እንደምንረዳው በተለይ የአባቷን ዱካ በመከተል ከሌሎች ልጆቻቸው በተለየ መልኩ የቅርብ ታዛዣቸው መሆኗን ከታሪኩ እንረዳለን፡፡ በአንድ ወቅት ጄነራል ፍራንኮ እቤታቸው ቁጭ ብሎ ሣለ ከአርበኞች መልዕክት  ይዞ የመጣ  ደበሎ የለበሰ ለማኝ የሚመስል ሰው በራፋቸው ላይ ቆሞ ሲለምን ሚስጢሩን የተረዱት አባቷ “አቶ በሼ ቀስ ብለው ለሽንት እንደሚወጣ መስለው ሴማዊትን ካገኙ በኋላ ደበሎ የለበሰውን ሰው ከየት እንደመጣ ማን እንደላከው ማንን ማገኘት እንደሚፈልግ ጠይቃ እንድትረዳ አዘዟት /የጠፍ ከዋክብት፣6/ ደራሲው የአባቷን ትዕዛዝ በቅልጥፍና መፈፀሟን እንዲህ ሲል ይገልፃታል፡፡ ‹‹ቀልጣፋዋ የበሼ ቆንጆ የታዘዘችውን ፈፀመችና ጠራቻቸው የመጣበትንም አላማ አስረዳቻቸው /የጠፍ ከዋክብት፣6/

ከዚህ እንደምንረዳው ሴማዊት የአባቷ ቀኝ እጅ ትዕዛዛቸውን ያለማወላወል የምትፈጽም መሆኗን ነው፡፡ ሌላው የሴማዊት ህሊናዊ አቀራረጽ ከባንዶች ጋር በመወገን አባቷንና ቤተሰቧን ሊያጠቃ ያላሰለሰ ጥረት የሚያደርገውን ኪዳኔ የተባለ ባንዳ ገፀባህሪይ እንዴት አርጋ እንደምትመልሰውና ብሎም በራሣቸው በጣሊያኖቹ ትዝብት ውስጥ እንዲገባና እንዲሸማቀቅ የምታደርግበት መንገድና ብልሃቱን ደራሲው እንደሚከተለው ያስነብበናል

“ ስሚ አንቺ እሱ ጋር ምን ታደረጊያለሽ” ጠየቀ የወታደሮቹ አዛዥ

“ ምን እያደረጉህ ይመስልሃል

“ ነይ ወጭ” አላት

‹‹ ምነው እኔንም ትፈራኛለህ እንዴ? ቦንብ የምወረውርብህ መስሎ ከሆነ   ቦንብ የለኝም፡፡ በጣም የምታሣዝኑ ናችሁ፡፡” አለች

“ ለምን እናሣዝንሻለን›› ሲል ጠየቃት

“ አባቴን ካለመናችሁ ማንን ታምናላችሁ?” አለችው እስከትላም

‹‹የኔ አባት ለእናንተ ያለው ፍቅር ልዩ ነው እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የኔ አባት የሮማን መንግስት ከቤተሰቦቹ በላይ ነው የሚወደው፡፡፡ እናንተ ግን ለዚህ ውለታው እንደወሮበላ ግቢውን በጠመንጃ ወርራችሁ እና የሚወዳቸውን ውሾቹን በጥይት ደብዳባችሁ ገደላችሁ

የሚገርመው ግን ይህን ሁሉ የሀሰት ታሪክ የነገራችሁ ሰው ለምን እንዲህ እንደሚያደርግ አለማወቃችሁ ነው…ብላ ሳትጨርስ አንደኛ ው አቋረጣት፡፡የሐበሻ ሰው ነው፡፡ “ለምንድን ነው” ሲል አንባረቀባት፡፡

“ይሄ ኪዳኔ የሚባል ሰውዬ አባቴን ይጠለዋል፡፡ የሚጠላውም እኔን አልድር ስላለው ነው፡፡ ኪዳኔ እኔን ላግባ ብሎ ሲጠይቅ እኔ ቀድሜ ታጭቼ ስለነበር አባቴ አይሆንም ብሎ ምክንያቱንም ነገሮ ጥያቄው ሊሣካለት እንደማይችል አስረዳው /የጠፍ ከዋክብት፣33፣34/

“ይሄ ሰው ግን እኔን ጠለፈኝ፡፡ ያን ጊዜ ደግሞ ወንድሞቼን ተናደዱና እሱን ደበደቡት፡፡›› ኪዳኔን አየት ስታደርገው “ውሽቷን ነው ” ለማለት አቆብቆበ እድል ግን አልሰጠችም፡፡እሷ ንግግሯን ቀጠለች፡፡

“ወታደሮቹ ደግሞ ሌላም የምትነግራቸው ነገር እንዳለ ሁሉ እየጠበቋት ነው፡፡ በተለይ ወታደሮቹን የሚመራው ነጩ ወታደር ተመሰጦባታል፡፡”

“ኪዳኔም የዋሸችበትን እንኳን ለማስተባበል መሞከሩን ትቶ ሌላ ምን ልትል ይሆን ሲል ተመስጧል፡፡. . .”

“ከዚያም ወደ ኪዳኔ ላይ አፈጠጠች፡፡ እባክህ! እባክህ! ኪዳኔ ወንድ ከሆንክ እኔን እሣምነህ ልታገባኝ ትችላለህ ባሌን አሁን ፈትቼዋለሁ፡፡ ንፁህ አባቴን ማጥቃትህን ተው አለችው፡፡” /የጠፍ ከዋክብት ፣34/

ኪዳኔ ሣያስበው አንድ ቃል አመለጠው፡፡ “አዝናለሁ” ሲል

ፈጣኗ ሴማዊት ጨዋታውን ተጫወተችው፡፡በፍጥነትና በቅልጥፍና በልስላሴ /የጠፍ ከዋክብት ፣35/

“ምንም አይደል የእስካሁኑ በደልህን እርሳው ከአሁን በኋላ ግን በውሸት በደል ባባቴ ላይ አትስራ፡፡ ያኔ ወንድምቼ የደበደቡህንም ቢሆን እርሣው፡፡ ካሁን በኋላ እኔና አንተ ጥሩ ወዳጅ እንሆናለን፡፡” አለችው

“ወታደሮቹ ዞር ብለው አፈጠጡበት፡፡ መልስ አስኪሰጣቸው እንኳን አልጠበቁትም ጥለውት ውልቅ ውልቅ እያሉ ወጡ ፡፡ በተለይ አዛዡ እብድ ነው የሆነው፡፡ . . . የወታደሮቹ አዛዥ እየተጠዳፈ እየወጣ “ ይቅርታ አቶ በሼ!” አለ፡፡

አቶ ኪዳኔም አንገቱን አቀርቅሮ ወጣ፡፡ “አዝናለሁ” ብሎ የተናገራት ቃል እንዴት ይሄን ሁሉ ውድቀት ልታመጣበት እንደቻለች እያሰበ . . . ፡፡”

ይህች ለስላሳ እባብ ግን በፍጥነት እና በቅልጥፍና ጉድ ሰራችው "የበሼ ልጅ መሆኗን መርሳት የለብኝም ነበር።" አለ በምሬት ኪዳኔ ።/የጠፍ ከዋክብት፣ 36/

ይህ ሲታይ ሴማዊት ነገሮችን ከነገሮች አቀናጅታ አባቷን እንዲሁም አርበኞችን ከጥቃት ስትከላከል እናያታለን። ከዚህም ሌላ ጀግንነቷ እንደ አካላዊ መልኳ ነው።፡ ይህ ሲባል በሴትነቷ ጫካ ገብታ  መዋጋት እንደማትችል የአጐቷ ልጅ ተፈሪ ቢነግራትም የጀግንነት ሥራዋን ከመስራት ግን ወደኋላ አለማለቷን ልብ ማለት ይቻላል። በተለይ በመጀመሪያዎቹ የወረራ ወቅት"..... ባሏን ሰረቀኃይል ወኔውን ቀስቅሣ ወደ ተፈሪ ጦር ቀላቀለችው። ባሏን ብቻ ሣይሆን ሌሎች ወንዶችንም እየቀሰቀሰች የተፈሪ ተከታይ አድርጋዋለች።" /የጠፍ ከዋክብት፣35/ ይህ እንደሚይስረዳው እራሷ መሽፈት ባለመቻሏ የምትወደውን ባሏን ከራሷ ፍቅር የአገር ፍቅር አስበልጣ አሸፍታዋለች። "ሴማዊት እራሷ ወንድ ሆና ባለመወለዷ ትቆጫለች፤ ጀግና  ደግሞ ትወዳለች። ተፈሪ  ደግሞ ለእርሷ ጀግና ብቻ ሣይሆን ወንድሟ፣ ሚስጠረኛ ወዳጅ የባህሪው ፎቶ ኮፒ ለመሆን የምትጥርለትና ተንከባካቢዋም ነው። የተፈሪን ሽፍትነት ስትሰማ አብሬ እሽፍታለሁ አለች። ተፈሪ ተቆጣት። ሆኖም በልቧ ከሸፈተች ዘመን የላትም። ከተፈሪ ጋር።"/የጠፍ ከዋክብት፣35/ ታሪኩ እንደሚያስረዳው ምን ያህል ቆራጥና አስተባባሪ መሆኗን ነው። እንደውም ባንድ ወቅት ተፈሪ ያለበት ድርስ መሄዷን ታሪኩ ይነግረናል።

"ለምን መጣሽ ?" ድጋሚ ጠየቃት

". . . ይህን ልናደርስልህ ነው የመጣነው።›› ስትል መለሰችለት። ተፈሪ ግን "ይሄን እማ ለማድረስ እናንተ መልፋት የለባችሁም።" ሲል በቅሬታ መለስላት መልሷ እንዳላረካው የተረዳችው ሴማዊት /የጠፍ ከዋክብት፣84/

ከአንተ ጋር መሆን ፈልገን ነው የመጣነው እሱንማ ተነጋግረናል›› . . . /የጠፍ ክዋክብት፣85/

‹‹. . . . ሆኖም ተፈሪ ሁለቱም መሄድ እንደላባቸው የግድ ስላላቸው ሁለቱም ለመሄድ ተሠናዱ።" /የጠፍ ከዋክብት፣107/

ከዚህ በተጨማሪ በውበቷ የተማረከው ጄነራል ፍራንኮ እቤታቸው በመጣበት ወቅት በጣሊያኖችና ባንዳዎች ስለተቋቋመው አርበኞች ግንባር አባሎች ስልታዊ በሆነ መልኩ ስታናገዘው ከታሪኩ እንረዳለን።

ከዚህ በተጨማሪ ምንም እንኳ ጫካ ገብታ ባትዋጋም የሰላ አእምሮዋን በመጠቀም ጫካ ካሉት  አርበኞች እኩል ለአገሯ ነፃ መውጣት የምታደርገውን ጥረት ታሪኩ እንዲህ ሲል ይገልፃታል፡፡

> "እንደማንኛውም ብልህ አርበኛ በኢትዮጵያ ላይ እየደረሰ ያለውን ሰቆቃ እርሱ ከሚጠብቀው በላይ ጠንቅቃ ታውቅ ነበር፡፡ እንደ ባላባት ልጅነቷ የቄስ ትምህርት ተምራና ዳዊት ደግማ ነው ባል ያገባችው፡፡እንደ አርበኝነቷ እና እንደ አርበኛ ልጅነቷ ደግሞ በየጊዜው በየቀኑ ስለሀገሯ ብዙ ነገር ትሰማለች ብዙሪያዋ ምን እንደሚካሄድ ታወቃለች፡፡/የጠፍ ከዋክብት/

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳ እሷም አርበኛ መሆኗን ያስገነዝበናል በመረጃ በኩልም በውበቷ የተማረከው ጄነራል ፍራንኮን የጣሊያን ተቆርቋሪ በመምሰል ሚስጢራዊ መረጃዎችን ታስወጣዋለች፡፡ በተለይ በጣሊያኖችና በባንዳዎች የተቋቋመውን የአርበኞች ግንባር ሥራና አባላቶች ላይ ትኩረት በማድረግ፡፡ በዚህ ትኩረቷም የሚያስደነግጥና ልታምነው የከበዳት ነገር ግን የተደረገ ሚስጢር ከጄነራሉ ትሰማለች ይኸውም ባሏ ሰረቀኃይል የአርበኞች ግንባር አባል መሆኑንና  በዚህም ምክንያት ምን ያህል ሞራሏ እንደተነካ ታሪኩ እንዲህ ያስነብበናል".. .እንደዚህ  ልፍስፍስ ባል ከሚኖረኝ ሺህ አመት ያለባል ልቀመጥ አለች ሴማዊት፡፡ የሚያፈቅሩትን መጥላት የሚጠሉትን ከመጥላት ጠንካራ ነው፡፡ ጥላቻ ህሊናን እንኳ የማሣት ሀይል አለው፡፡ በሰረቀኃይል ላይ የተሰማት ጥላቻ ሀያል ከመሆኑ የተነሣ አሁኑኑ ጠፍቶ ልታየው ፈለገች፡፡ /የጠፍ ከዋክብት፣187/ ይህንንም ምኞቷን ለማሣካት ጄነራሉን በመጠቀም  የሚገናኙበት መንገድ ታመቻችና እርምጃ ለመውሰድ ትዘጋጃለች ይህ ቁርጠኛ አቋሟን ታሪኩ እንዲህ ያስነብበናል፡፡ሴማዊት እሰረቀኃይል ላይ እንዳፈጠጠች "አንተ ውሻ! ልክስክስ! ስትል" ካጠለቀችው የወንድ ኮት ኪስ ውስጥ ሽጉጥ አውጥታ አነጣጠረችበት "ንቅንቅ ትልና!" በማለት አስጠነቀቀችው፡፡ /የጠፍ ከዋክብት፣196/

> እንደማትምረው ሲያስብ ፍርሃት ዋጠው፡፡ ያነገተውን መሣሪያ በፍጥነት አውልቆ ሊጠቀምበት ፈለገ፡፡ ግን እንደዚያ አይነት ሙከራ ቢያደርግ እንደምትቀድመው ያውቃል‹‹ አንተ ባንዳ ወንድሜን ከዳኸው፣ ኢትዮጵያን ከዳሃትና ለጠላት አጎበደድህ፡፡ ፍቅሬንም ረግጠህ፡፡ ቃል ኪዳንህን በጭቃ ለወስህ ቀበርከው /የጠፍ ከዋክብት፣196/

ከሩቅ ሰው መምጣቱን የተረዳችው ተኮላ አማራጭ በፍጥነት ወሰደች በሰረቀኃይል ላይ በግንባሩ ለቀቀችበት ደገመችው ለሶስተኛ ጊዜ ተኮሰች፡፡/የጠፍ ከዋክብት፣196/

በዚህ ብቻም አላበቃም ሠረቀኃይልን ሊያስጥለው የመጣውን ምክትል ጄነራል ሲልቪዩ ለተኮሰባት ጥይት አፀፋውን ስትተኩስ ይስተዋላል፡፡ ይህም ምን ያህል ቆራጥና ጀግና ለአላማዋ ፅናት፣ ለኢትዮጵያ ነፃነት በብልሃትና በቆራጥነት ማድረግ የፈለገችውን የምታደርግ ጀግና ገፀባህሪይ ተደርጋ የተሣለች ናት፡፡ ለዚህም አብነት ይሆነን ዘንድ ከሠረቀ ኃይል ሌላ ምክትል ጄነራሉ ላይ የወሰደችው የተኩሰ አፀፋ ታሪኩ እንዲህ ያስነብበናል፡፡ ምክትል ጄነራሉ በተወሰነ ርቀት ተዘርሯል፡፡ ሴማዊት የተኮሰችው ጥይት ደረቱን መታው /የጠፍ ከዋክብት፣201/ ታሪኩ እንደሚያስረዳው በተኩስ ልውውጡ ወቅት ሴማዊትም መመታቷና መሞቷን ነው ይህም ዋቢ የሚያደርገው ለአላማዋ እስከ ሞት መስዋእትነት የከፈለች ጀግና ሴት መሆኗን ነው፡፡

### 3.2.2.2 የጄነራል ፍራንኮ ህሊናዊ አሳሳል

የጄነራል ፍራንኮ ህሊናዊ አሣሣል በበቀለኝነት፣ በንቀት፣ በሴሰኝነትና በሞኝነት የተሞላ ነው፡፡ ጄነራሉ ፍራንኮ አገሩ የጣለችበትን ግዳጅ ለመወጣት በአውሮፓዊ ኩራትና ከኛ በላይ ሰው ላሳር በሚል ትምክህት አባቶቹ ያጡትን ክብር እርሱ ለመመለስ ብሎም ሊበቀልላቸው ቃል ገብቶ አገሩንና ወገኑን ክብር ለማጕናፀፍ ቆርጦ የመጣ ጄነራል ነው፡፡ ደራሲውም እንዲህ ያብራራዋል "አየህ እነዚህ ህዝቦች  በቅኝ ግዛትነት ብቻ አይደለም ልንገዛቸው የሚገባው፡፡ ልንበቀላቸውም ይገባል፡፡ ምክንያቱም አዋርደውናል በአለም ፊት አስቀውብናል /የጠፍ ከዋክብት፣9/ ሲል ጄነራሉ ለምክትሉ ሲያስረዳ ይነበባል፡፡ ለዚሁም አባባሉ ደራሲው በተለያየ የታሪኩ ቦታ ላይ ጄነራሉን ይገልፀዋል፡፡ በታሪኩ ሂደት የጄነራል ፍራንኮን በቀለኝነት የሚያሣዩ ጉዳዮች ተገልፀው እናገኛለን፡፡ ለተልዕኮው መሣካት ሲል አማራና፣ ኦሮምን በማጋጨት ትርፍ ለማግኘት የወጠነው ጄነራል ስለበቀል ያለውን ጥመኝነት እንዲህ ሲል ይደመጣል

ፍራንኮ " ምን ነካህ? ሲሲሊያዊ ደምህን ምን በረዘብህ"

‹‹. . . እኔ እንኳ ሲሲሊያዊ ደም የለኝም ግን እንደማንኛውም ኩሩ አውሮፓዊያን ጀግና ጠላቴን አስከመጨረሻ ከመበቀል ወደኋላ አልልም፡፡ ጠላትነትን በጣም አከብራለሁ በተለይ ያዋረደኝን ጠላት ሳልበቀል በፍጹም አላርፍም. . . ፣፡፡»/የጠፍ ከዋክብት፣9/

> "በብረት ምጣድ እየተጠበሰች እንኳን እንደ ሀያል ልጃ አልረታ ብላ ያስቸገረችውን ሴት ጄነራል ፍራንኮ ሞት ብቻ እንደሚረታት ሲረዳ ዞር ብሉ አቶ ኪዳኔንን እያየ "ኪዳኔ ልጃን መግደል ባትችልም እሷን እንኳን ግደላት፡፡" ሲል አዛዘው /የጠፍ ከዋክብት ፣ 218/

ከጥቅሱ እንደምንረዳው ሰብአዊ ስሜት ያልፈጠረበት ግብዝ፣ የሰው ስቃይ የሚያስ ደስተው፣ በቀለኛ እንደሆነ ከራሱ ከጄነራል ፍራንኮ እንደበት ይደመጣል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለሀበሻ ያለውን ንቀት ሲገልፅ "ኤዳያ! አንተ ደግሞ ሁል ጊዜ ጥቁር ህዝብ እንደ ነጭ የሚያስብ ይመስልሃል፡፡ ይህን ጥበብ እስኪ ከየት ሊካኑት ይችላሉ?" አለና አፈጠጠበት…፡፡ /የጠፍ ከዋክብት፣18/ ጄነራል ፍራንኮ ከምክትሉ ጋር በሚያደርገው እስጣ ገባ ስለኢትዮጵያዊያን አርበኞች ያለው ንቀቱ ጎልቶ ሲወጣ ያሳየናል፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞ ንቀቱንና የአገሩን የበላይነት የተፈሪን እናት በማሰቃየት እንዲህ ሲል ይደመጣል

> ጄነራል ፍራንኮ በጋለ ብረትምጣድ ላይ እየተጠበሰች ያለችውን የተፈሪን እናት በንቀት ቁልቁል እያየ "አንቺ ቆሻሻ ዛሬስ አመንሽ? የሮማን ሀያልነት ተረዳሽ? ከሀያሉ የሮማ መንግስት የሚያመልጥ እንደሌለ አወቅሽ" ሲል በንቀት ጠየቃት /የጠፍ ከዋክብት፣216/

ጄነራል ፍራንኮ ከበቀለኝነቱና ከንቀቱ ባሻገር ሴሰኝነቱም ይስተዋልበታል በዚህ የሴስኝነት ባህሪይው በመጠቀም በፍቅር የከነፈላት ሴማዊትና ከነተፈሪ ጋር ደም ተቃብተዋል ብሎ የሚያስባትን አልባስወርቅ ባለው የፍቅር ግንኙት እንደፈለጉ ሲያሽከረክሩትና የተዛባ መረጃ በመስጠት ለጥቃት ሲያመቻቹት ይታያል፡፡ ይህ ባህሪይው የተወለደው ለኢትዮጵያ አርበኞች ካለው ንቀትና ሴስኝነት ሲሆን ይህንንም በመረዳት በፍቅር የቀረባቸው ሴቶች ሲጠቀሙበትና የድል ሚዛን ወደ አርበኞቹ እንዲሆን ሲያደርጉ ይታያል፡፡ ጄነራሉ ሴሰኝነቱን ደራሲው እነዲህ ያረጋግጥልናል፡፡ "ጄነራሉ ሴት በመውደዱ በኩል ተብሎ ያለቀለት ነገር ነው ሴት ይወዳል፡፡ ቀሚስ የለበሰ ካየ ጭናቸውን የሚያስበው ገልቦ እንጂ ከዚያ ውጪ የሴትነት ባህሪያቸው አይታየውም፡፡/የጠፍከዋክብት፣18/ይልናሌላ ትንታኔ ይሰጣል ይኸውም‹‹የጄነራል ፍራንኮ ፍ ልስፍና እንደሚተነትነውና እንደሚያስተነትነው የሴት ልጅ ባህሪዋም፣ ልቧም፣ ጭንቅላቷም፣ ጥቅል እሷነቷም የሚገኘው ጭኗ ሲገለብ ነው፡፡" /የጠፍ ከዋክብት፣19/

ስለዚህም በቀላሉ የሚጠመድ ከወታደራዊ ሥነ-ሥርዓት ውጪ የሆነ ባህሪይ ጉልቶ የሚታይበትና ምንም ፍቅር የማያውቅ ከአገኘው ጋር ሁሉ የአሰኘውን የሚያደርግ እንደሆነ ከታሪኩ ለመረዳት ይቻላል፡፡

“እጎኗ ሄጄ ልቀመጥ” ብሎ ካሰበ በኋላ አንድ ቀን በፍልጥ ያነደደችው ታሰበውና ተወው ፈራት፡፡ ለነገሩ ሴት የሚፈራ አልነበረም በርግጥ ያፈቀረበትን ጊዜ ማስታወስ አይችልም ግን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሴቶች ተገናኝቷቸዋል ሁሉም ተራ እንደሆኑ ያስብ ነበር፡፡አጠገቡ የሚያገኛቸው ሴቶች ሁሉ ሲጠይቃቸው ብዙ አስቸግረውት አያቁምና፡፡ ከነጭ እስከ ጥቁር /የጠፍ ከዋክብት፣ 158/

ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ ሴሰኝነቱን በመጠቀም እርሱን አፍቃሪ መስለው የተዛባ መረጃ በመስጠት አገሩ የጣላችበትን ግዳጅ እንዳይወጣ ብሎም ጀግንነቱ እንዳይጐላ እኩይ ባህሪይዎቹ እንቅፋት ሲሆኑበት ይታያል፡፡

### 3.2.2.3 የምክትል ጄኔራል ሲልቪዬ ህሊናዊ አሣሣል

ምንም እንኳ ምክትል ጄነራል ሲልቪዬ አገሩ የጣለችበትን ግዳጅ ለመወጣት በቆራጥነትና በጀግንነት ለማገልገል ቢመጣም አስተዋይ፣ ተጠራጣሪ፣ ለጠላቶቹ ዝቅ ያለ ግምት የማይሰጥ ከአገሩ የመጣበትን ዓላማ ጠንቅቆ የሚያውቅ ተደርጎ የተሣለ ገፀ ባህሪይ ነው፡፡ በተለይ ስለኢትዮጵያዊና ስለ እምነታቸው ስለህዝባቸው አወቃቀር ከዋናው ጄነራል የተሻለ ዕውቀትና ግምት ያለው የጦር ሰው ነው፡፡ ስለዚህ ከነዚህ ዋና ዋና ህሊናዊ አሣሣል መሀል ስለ ኢትዮጵያዊያን ጀግኖች ጠንካራነት እንዲህ ሲል ተደምጧል“የሀበሻ ጀግኖች እንደ መናፈስት ናቸው”ሲል ተገረመ /የጠፍ ከዋክብት፣11/ ከዚህ በተጨማሪ በሚደረጉት ጦርነቶች ሁሉ በሚደርስባቸው ጥቃት መቋቋም እንደማይችሉና ከወታደራዊ ጥናቶች በመነሣት አለቃውን እንዲህ ሲል ይደመጣል፡፡

ሲልቪዬ፡ በድፍረት ጄነራል! ወታደራዊ ጥናቶቻችን ምን ድምዳሜ ላይ እንደደረሰ ባትረሳ መልካም ነው››

‹‹ምን ድምዳሜ ላይ ደረሱ የጐድን እያስተዋለ ጠየቀው፡፡

ሲልቪዬ፡ ወታደራዊ ጥናቶቻችን የደረሱበት ድምዳሜማ በአፍሪካ ምድር የሂትለር ጀርመንን ሠራዊት ሊቋቋም የሚችል ሠራዊት ሊመለመል የሚችለው ከሐበሾች መሃል ብቻ ነው የሚል ነው ሲል አስረዳው፡፡/የጠፍ ከዋክብት፣82/

ከዚህ እንደምንርዳው አገሩ ጣሊያንና ዋና አዛዡ ጄነራል ፍራንኮ ለኢትዮጵያ በድጋሚ ዝቅ ያለ ግምት መስጠታቸውንና የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት መርሣታቸውን ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ስለ ህዝቡ ኃይማኖትኛነት ጠንካራነትና አወቃቀር በሚገባ

የተረዳና መነጣጠል የማይችሉ ወጥ የሆነ አቋም ያላቸው መሆናቸውንም በሚገባ የተረዳ ገፀባህሪይ ነው፡፡ ይህም እንዲህ ሲል ይደመጣል፡፡"እኛም አጠቃናቸው ጥቃታችንን ደግሞ በባህላቸው፣ በታሪካቸውና በእምነታቸው ላይ ቀጠልን፡፡ እነዚህ ህዝቦች ደግሞ ጥንታዊ ታሪክ ያላቸው እና የደረጀ ባህል ሐይማኖት ያላቸው ህዝቦች ናቸው፡፡ ይህን ስትነካካባቸው ደግሞ ሞትን አይደለም ሲኦልን አይፈሩም፡፡"/የጠፍ ከዋክብት፣103/ ይሄ እንደሚያስረዳን ምን ያህል ስለኢትዮጵያዊያኖች የጠለቀ አመለካከት እንዳለው እንገዘባለን፡፡ ለዚህም ተጨማሪ ማስረጃ እንዲህ ሲል ይደመጣል፡፡ "ሮማ ጥንት ታላቅ በነበረችበት ስዓት በአለም ላይ ሌላዋ ታላቅ አገር አቢሲኒያ እንደነበረች ለምን ትዘነጋለህ?"/የጠፍ ከዋክብት፣104/ በመሆኑም ይህ ምክትል ጀነራል በሐይማኖትና በብሔር በመከፋፈል፣ ባህልና ወጓ ላይ በመዝመት የሚመጣ ምንም ለውጥ እንደማይኖር በመረዳት ስልታቸውን መለወጥ እንዳለባቸው ለአለቃው ጄነራል ፍራንኮ በድፍረት እንዲህ ያስረዳዋል፡፡

> "እስከሚገባኝ ስልታችንን መለወጥ አለብን እኛ ማድረግ ያለብን በዝግታ እና በፈቃደኝነት ባህላችንን ሐይማኖታችንን እና ታሪካችንን እንዲቀበሉ ማድረግ እንጂ በሀይል ላይ ተመስርተን ቤተክርስቲያናቸው -ን መበዝበዝ ሐይማኖታቸውን ማንቋሸሽ ታሪክና ባህላቸውን ማጥቃት መተው አለብን፡፡. . . ."፡፡ /የጠፍ ከዋክብት ፣ 104/

ስለዚህ በዚህና በተለያየ መልኩ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት መግዛት አዳጋች እንደሚሆን ቀድሞ የተረዳ ሰው መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ሆኖም ግን አገሩ ግዳጅ ሰጥተዋለችና ግዳጁን ለመወጣት የመጣ የጦር መኮንን ነው እንጂ ወገኖቼን ያዋረዱ ጠላቶቼ ናቸው ብሎ ለመበቀልና ለመዋጋት ፈልጐ የመጣ ወታደር አለመሆኑን ከአባባሉ እንረዳለን ይኸውም፡፡

ጄነራል ፍራንኮ"ሲሊለያ እኮ ቂሙን አይረሣም!››

" እና "ጠየቀ ሲልቡዬ

‹ ምን እና ትለኛለህ፡፡ . . . ጠላትነት በጣም አከብራለሁ በተለይ ያዋረደኝን ጠላት ሳልበቀል በፍጹም አላርፍም፡፡ እነዚህም ቢሆኑ እኮ

. . . ጄነራል ፍራንኮ ሀሣቡን ሣይጨርስ የጀነራሉ ምክትል ሃሣቡን አቋረጠው፡፡"

" እነዚህ ህዝቦች ጠላቶቻችን ናቸው እንዳትለኝ" ሲል ሲልቪዬ ጠየቀ /የጠፍ ከዋክብት፣9/

ከዚህ እንደምንረዳው አገሩ የምታራምድው ፖለቲካ ልክ አለመሆኑን የተረዳ የጦር መኮንን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንድ የጣሊያን መነኩሴ ጋር የሚያደርገው ቃለ ምልልስ ይህንኑ ያረጋግጥልናል፡፡

> “. . . እውን እነዚህ ህዝቦች ጠላቶቻችን አይደሉም” ሲል ጠየቃቸው፡፡ ም/ጄነራል ሲልቪዬ ቄሱ በተገርሞ አዩት እናም በተራቸው ጠየቁት፡፡
>
> “ አንተ ምን ትላለህ” ሲሉ
>
> ‹ እኔ እንኳ እኛ ሳንሆን አንቀረም የእነርሱ ጠላቶች አለ፡፡”
>
> “ ቅን መንፈስ ያለህ ሰው ሳትሆን አትቀርም፡፡”አሉ የካቶሊክ ቄስ ጆን

በመሆኑም ይህን የጠላትነት መንፈስ ይዞ የመጣው የጣሊያን የወራሪነት ፍላጐት መሆኑን በሚገባ ያወቀና የተረዳ ሰው መሆኑን ልብ ማለት ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጐን ለጐን ደግሞ ወታደራዊ ብልጠቱንና ተጠራጣሪነቱን ብሎም በሚያደርገው ክትትል የሽንፈታቸው ምንጭ ዋናው ጄነራል ፍራንኮ የጣሊያን ወዳጅ ያላቸውን ሰዎች የጣሊያን ጠላቶች ናቸው በማለት የሚያደርገው ፍጥጫ እንደሚከተለው ይተነተናል . . ጠላትህን ወዳጅ አድርገህ በጉያህ እስከያዝክ ድረስ፣ የማይጨበጥ እቅድ እስከ ያዝክ ድረስ አሁንም ተሸናፊ አንተ ነህ” በድፍረት ጄነራል ፍራንኮን ወቀሰው /የጠፍ ከዋክብት፣78/ ይህን ያለበት ምክንያት በጦርነቱ በተከታታይ የደረሰባቸውን ሽንፈት መሠረት አርጎ ነው፡፡

ዋናው ጄነራል ማነው ጠላቴ? ማነውስ ወዳጄ ብሎ በሚጠየቅበት ወቅት “ጠላቶችህ በሼ ከነቤተሰቦቹ፣ አልባሠወርቅ፣ፒከሎና ገብርአብ ናቸው፡፡ ወዳጆችህ ደግሞ ኪዳኔና ፊትአውራሪ መነሻ ናቸው፡፡ ሲል ምክትል ጀነራል ሲሊቪዬ አብራራለት /የጠፍ ከዋክብት፣70/ ታሪኩም እንደሚያመለክተው በትክክል እውነተኛ ጠላቱንና ወዳጁን ያለየው ዋናው ጄነራል ሲሆን ይህም በተደጋጋሚ በተደረገው ጦረነት ሽንፈት የቀመሰው በአቶ በሼ የውስጥ አርበኝነት ብልሃት መሆኑን ልብ ይላል፡፡ ይህም ምክትል ጄነራሉ የደረሰበት ግን ማስረጃ ያጣበት ብሎም በዋና ጄነራሉ ሃሣቡ ውድቅ እንደሆነበት ብንረዳም በተጠራጣሪነቱ ደግሞ ለአርበኞች የሚደረጉ እገዛዎችን ለማኮላሸት የሚያደርገውን ጥረት እንደሚከተለው ይተነተናል፡፡

> ‹‹. . . እውነት ነጭ የሚባል ህዝብ ብልህ ነው እሚባለው ነጭ ሁሉ እንደዚህ ምክትል ጄነራል ከሆነ ነው፡፡ ምንም ነገር አያመልጠውም፡፡ ፊትህ ላይ አንብቦ ሆድህን ያውቃል፡፡ በውስጥህ ያለውን ሰርስሮ ለማወቅ ብቃት አለው፡፡ የሚደንቀው ግን ጄነራሉ

የዚህን ምክትል ጄነራል ብልህነት አውቆም ይሆን ሣያውቅ እንዲ ደበዝዝና ውጤታማ እንዳይሆን ያደርገዋል…።”/የጠፍ ከዋክብት ፣143/

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ለአርበኞች የሚደረገውን ዕገዛ ለማስተጓጐል ጥረት እንደሚያደርግ ነው፡፡ አቶ በሼ ልጃቸው አስፋውን ለአርበኞች ስንቅና መሣሪያ አድርሶ እንዲመጣ ልከውት ሣለ የተጫኑትን ፈረሶች ሲይዝበት ስለ ምክትል ጀነራሉ ያለውን ለአብነት እንጥቀስ፡፡

> ‹‹ ምነው ቶሎ መጣህ? በደህናህ ነው›› አባት ልጃቸውን ጠየቁ በደህናዬ ሣይሆን ጭኘው የነበረውን መሣሪያና ሰንቅ ጣሊያኑ ይዞብኝ ነው የመጣሁት፡፡ ያ የተረገመ ምክትል ጄነራል እያለ ጤና የለም /የጠፍ ከዋክብት፣145/

የአቶ በሼ ልጅ አስፋው ምሬት የሚያሣየው ምክትል ጄነራሉ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ነው፡፡

### 3.2.2.4 የበሼ ህሊናዊ አሳሳል

አቶ በሼ ባላባት፣ ሀብታም፣ ጥቃትን የማይወዱ፣ አልገዛም ባይ፣ ሁለት መልክ ያላቸው አንደበተ ርዕቱ፣ ጠንቃቃ፣ ቆራጥ፣ አገር ወዳድ፣ ሃይማኖተኛ፣ ስልጣኔ ወዳድ ሆነው የተቀረፁ ገፀባህሪይ ናቸው፡፡

በሸዋ ጁሩ አካባቢ የሚኖሩት በሼ ጣሊያን ኢትዮጵያ አገራቸውን በመውረሩ ምክንያት የውጊያ ስልታቸውን ጣሊያኖች አፍንጫ ሥር ሆነው ለመዋጋት በነደፉት ስልት መሠረት ፍጹም የጣሊያን ወዳጅ መስለው ጫካ ላሉ አርበኞች የመረጃ፣ የቁሣቁስና ስንቅ አቅርቦት የሚያደርጉ ሰው ናቸው፡፡ እነዚህን ሁሉ ድጋፍ ለማድረግ ብሎም አገራዊ ግዴታን ለመወጣት የወጠኑት ውጥን ይህን ይመስል ነበር፡፡

> “በሼ የነገር አካሄዱ ገና ከጅምሩ የሚገባቸው ነበሩና ኢትዮጵያ እጃን በጣሊያን እንደተያዘች “ አልተለመደም ” ባይ ልጆቿ ዱር ቤቴ ያሉ ጊዜ ነው ነገሩ ግልፅ የሆነላቸው፡፡. . . እሳቸው ደግሞ አብረው እንደይሸፈቱ እርጅና እጃቸውን ይዟቸዋል፡፡ ያ ብቻ አይደለም፡፡ /የጠፍ ከዋክብት ፣25/

ሽፍተነት ጫካ ብቻ እንዳልሆነ ብልሁ ሰው ብዙ ያውቃሉ፡፡
እጠላት አፍንጫ ሥር ሆነው ሽፍትነት እንዳለ ተገንዝበውታል፡፡»/
የጠፍ ከዋክብት፣25/

በመሆኑም አቶ በሼ ከጣሊያኖች ያገኙትን፣መረጃ የጦር መሣሪያና ስንቅ በጫካ ላሉ ኢትዮጵያን ነፃ ለማስወጣት ለሚዋጉ አርበኞች በማቀበል ድጋፍ የሚያደርጉ ገፀባህሪይ ተደርገው የተቀረፁ ናቸው፡፡ በአንድ ወቅትም የአቶ በሼ ልጅ አስፋው ለአርበኞች ስንቅና የጦር መሣሪያ ጭኖ ይዞ ሲሄድ የጫናቸውን ፈረሶች ምክትል ጄነራል ሲልቪዬ ይይዛቸዋል፡፡ ምክትል ጄነራሉም እንዲህ ሲል ይገልፃል፡፡ “ይህን ስንቅና መሣሪያ ማን እንደላከው ለማን እንደተላከ ባያቅም ይህን ያህል የመሣሪያና የስንቅ ዝግጅት አድርጎ ዱር ቤቱ ላለ ሽፍታ የሚልክ ጥሩ የሀብት አቅም ያለው፣ ጥሩ ወኔ ያለው እና ወደ ራሣቸው ወደ ጣሊያኖች አፍንጫ ሥር የተጠጋ ሰው መሆኑን ተረድቷል፡፡/የጠፍ ከዋክብት፣142 /ከዚህ እንደምንረዳው ይህንን የማድረግ አቅምና ወኔ ያላቸው አቶ በሼ ብቻ ናቸው፡፡

አቶ በሼ ራሣቸው አዘጋጅተው የላኩትን ስንቅና የጦር መሣሪያ ማን እንደላከው በሚያጣራው ኮሚቴ ውስጥ ሲካቱቱ ያሣየናል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ለጣሊያኖች በተለይ ለዋናው ጄነራል ፍራንኮ የቅርብ ወዳጅ መሆናቸውን ነው ይህንንም ደራሲው እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡፡ “ስለሆነም የዚህን ሰው ማንነት ለመለየት አጣሪ ኮሚቴ ማዋቀር ጀመሩ ሆኖም ጄነራል ፍራንኮ አቶ በሼም አጣሪ ኮሚቴ ውስጥ መግባት አለባቸው ብሉ ድርቅ አለ፡፡ /የጠፍ ከዋክብት፣ 142/

ከታሪኩ እንደምንረዳው አቶ በሼ ጣሊያኖችን በተለይም ከዋናው ጄነራል ጋር ያላቸውን ቅርበት ያሳየናል፡፡ እናም ባላቸው የማሣመን ችሎታ አገራቸውንና ወገናቸውን ነፃ ለማውጣት በሚያደርጉት ትግል ታሪኩ ውስጣዊ ማንነታቸውን፣ቆራጥ ሰብዕናቸውን ይነግረናል፡፡

የአቶ በሼ ሌላው  ህሊናዊ መልክ አሣሣላቸው ለስልጣኔ ያላቸው ጉጉት ምን ያህል እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡ “ይኸውም ከነጮቹ ጋር በዋሉ ቁጥር ስለ ስልጣኔ ይጠይቋቸዋል፣ ስለፋብሪካ፣ ስለማዕድናት፣ ስለዘመናዊ ግብርና፣ ስለዘመናዊ የውጊያ ስልት እና ስለሌሎች ስልጣኔ ስለወለዳቸው ነገሮች አንስተው ሚስጥሩን ለማወቅ ይሞክራሉ፡፡ ሁሉም በፅንሰ ሃሣብ ደረጃ ቀላል ሆኖ ይታያቸዋል፡፡ከባድ ሆኖ የሚያገኙት ግን  አተገባበሩ ነው፡፡/የጠፍ ከዋክብት፣4/ ለዚህም ካላቸው ጉጉትና ፍላጎት እንዲህ ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ “ህዝብን ወደ ስልጣኔ ጎዳና ሊወስድ የሚችለው ጀግና ወይስ ጠቢብ

መሪ? ሲሉ እራሣቸውን ይጠይቃሉ፡፡" /የጠፍ ከዋክብት፣4/ በመጨረሻም ስለአተገባበሩ ጠቢብ የሆነ ሰው ሲያነጋግሩ እናያለን ይኸውም፡፡

> "እነዚህ የተከበሩ ጠላቶች የሰሩትን ጠመንጃ እዚሁ ሀገር ቤት ባለ ጠበብት መስራት እንደሚቻል አቶ ስዩም የሚባለውን ታዋቂ ጠቢብ እና አርበኛ አስጠርተው አነጋገሩ እርሱም ይህንንም ጠመንጃ አስመስዬ አስራዋለሁ፡፡" ሲል መለሰላቸው" /የጠፍ ከዋክብት፣5/". . . ሆኖም በስዩም መሪነት የሚሰራው መሣሪያ እንደ ተከበሩ ጠላቶቻችን የሚጮህ ጠመንጃ ሆነ ፡፡/የጠፍ ከዋክብት ፣5/

አቶ በሼ ጣሊያኖችን የተከበሩ ጠላቶቻችን ሲሏቸው ይደመጣል፡፡ ስልጣኔቸውን በማድነቅ የተከበሩ ሲሏቸው ወራሪነታቸውንና ግፋቸውን በማየት ደግሞ ጠላቶቻችን ይላቸዋል፡፡ ጠላትን ካገሪቱ ጠራርጐ ለማውጣት ደግሞ በነደፉት ስልት ሲዋጉ እናያለን፡፡ከዚህም ሌላ የአገሬው ሰው እንዲሁም ጣሊያኖቹ በእርጋታቸውና በማሣመን ችሎታቸው ይደነቃሉ ስለዚህም ከታሪኩ እንደምንረዳው እንዲህ ተገልጿል፡፡ "እርጋታ የሚነበብባቸው እንደረጋ ወቅያኖስ ጥልቀታቸው የማይደርስበት ሰው ናቸው›› በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን በዙሪያቸው ያለን ሁሉ የማሣመን ተሰጥኦ አላቸው /የጠፍ ከዋክብት፣24/በመሆኑም በቆራጥነታቸው ከአስመሣይነታቸው ባለፈ ተናግሮ አሣማኝ መሆናቸው ልብ ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህም ሌላ ጠላትን ወዳጅ ለማድረግ ቂም የያዘባቸውን የጣሊያን ባንዳ የሆነው ኪዳኔ ይቅር ለመባባል የሚያደርጉትን ጥረት ታሪኩ እንዲህ ይገልፀዋል፡፡"አቶ በሼም የኪዳኔን ጠላትን ሊያባብሱት አልፈለጉም ነበርና አንድ ቀን ለብቻው አስጠርተው አነጋገሩት፡፡ በቅንነት እና በትህትና እንዲህ አሉት" /የጠፍ ከዋክብት፣25/

> ለመሆኑ አቶ ኪዳኔ ምን እደረግሁህ? ምንስ በደልኩህ ምን ያስቀየምኩህ ነገር አለ? አንተ ለኔ ንጹህ ወንድሜ ነህ፣ አንድ የነብስ አባት አለን፣ ሁለታችንም ክርስቲያኖች ነን፣ የአንድ አገር ሰዎች ነን ዘመዶቻችን እርስ በእርሳቸው ተጋብተዋል፣ መጋባት ብቻ ሣይሆን ተዋልደዋል እና ለምን እኔን ሁል ጊዜ በጣሊያኖች ላይ ትከሰኛለህ? ሲሉ ጠየቁት? /የጠፍ ከዋክብት፣26/

አቶ ኪዳኔም ለብቻው አነጋግረውት ምን እንደበደላቸው ጠይቀው እርቅ ለመፍጠር ቢሞክሩም በአቶ ኪዳኔ እምቢ ባይነት እርቅ መውረድ ሳይችል ቀረ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ ሙከራ አደረጉ፡፡ የአቶ ኪዳኔን ወዳጅነት እንጂ ጠላትነት ስለማይፈልጉት፡፡

"አቶ በሼ በተፈጥሮአቸው ማንም ጠላት መሆን የለበትም ብለው ያምናሉ፡፡ በጠላትነት ምን ትርፍ ይገኛል፡፡ ወዳጅህ ግን መከበሪያ መሸሸጊያና ቀኝ እጅህ ሊሆንህ ይችላል፡፡ እና ጠላት ቢኖርህ እንኳ ወዳጅ አርገው፡፡ የሚል የራሣቸው ቢሂል አላቸው ስለዚህ አቶ ኪዳኔ ለአማላጅነት የጋራ የነብስ አባታቸውን መምሬ በዙን ላኩ /የጠፍ ከዋክብት፣29/

> መምሬ በዙ ሁለት የነብስ ልጃቻቸው እንዲታረቁላቸው የተቻላቸውን ሁሉ ጣሩ አገናኝተውም ሲያነጋግሯቸው በሼ በነብስ አባታቸው ፊት ለስለስ ብለው እንዲህ ሲሉ ተናገሩ ወዳጄ አቶ ኪዳኔ በል እስቲ ዛሬ ንገረኝ የነብስ አባታችን ባሉበት አጫውተኝ፣ ለምንስ ጠላቶች እንሆናለን? በእርግጥ እኔ አሁን አንተን የማይህ ወዳጄ እንደሆንህ ሁሉ ነው ያንተን ግን አላውቀውም ሲሉ ተናገሩ፡፡

ሆኖም ግን አቶ ኪዳኔ ይቅር ሊላቸው አልቻለም፡፡ በመሆኑም አቶ በሼ ይቅር በመባባል ማስወገድ የፈለጉትን የጥላቻ መንፈስ ማስወገድ ባይችሉም ለይቅርታ ረዥም መንገድ መጓዛቸው ምን ያህል ሰላም ወዳድነታቸው ከመመስከሩም ባሻገር ጠላታቸውን ወዳጅ በማድረግ የማያቋርጥ መረጃ ስንቅና የጦር መሣሪያ ማግኛ መንገዳቸው እንዳይነጥፍ ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡

በመጨረሻም በሚስጢር ታግለውና አታግለው አገሪቱ ነፃ ብትወጣም ያልገመቱትና ያላሰቡት ነገር የገጠማቸው በሼ አዝነውና ተከፍተው እናገኛቸዋለን፡፡ የተከፉበት አንዱ ምክንያት ደግሞ ይቅርታ ጠይቀውና አስጠይቀው አሻፈረኝ ያላቸው ባንዳው ኪዳኔ ጣሊያን አገሪቱን ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት ያደረሰባቸው በደል አገሪቱ ነፃ ስትወጣ ተፈሪን ከንጉሱ ዘንድ በመክሰስ እንዲሞት በማድረጉ ለመግደል ሲሰናዱ ታሪኩ እንዲህ ይነግረናል‹‹.. . . አቶ በሼ ድንገት ከኋላው ብቅ አሉና የያዙትን መሣሪያ ኪዳኔ ላይ አነጣጠሩ›› /የጠፍ ከዋክብት ፣236/ ይህን ለማድረግ የተገፋፉት ነፃ በወጣችው ኢትዮጵያ ለጣሊያን በመወገን እንደ ኪዳኔና መሰሎቹ ያሉ ሰዎች ተሹመውና ተሸልመው ሲያዩ፣ በአንፃሩ ለኢትዮጵያ ነፃነት በዱር በገደል ተዋግተው ነፃ ያወጧት እንደ ተፈሪ ያሉ ቁርጠኛ ልጆቿ እንደ ባንዳ ታይተው በወታደር ተከበው ሲረሸኑ በማየት በጥልቅ ሀዘንና ምሬት ኪዳኔን ሲናገሩት ይደመጣል፡፡

> ‹‹ ኪዳኔ እህቴን የገደልክ፣ ተፈሪን ከባንዶች ጋር ሆነህ በንጉስ ዘንድ እንዲጠላ ነገር የሰራህ፣ ውሾቼን ያስገደልክ በጠላት በተደጋጋሚ ያጠቃኸኝ ለሴማዊት መገደል ሰበብ የሆንክ በዚህ አለም ላይ ያለኝን ነገር ሁላ እንዳጣ ያደረግኸኝ ሰው ነህና ልገልህ ይገባል /የጠፍ ከዋክብት፣236/

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ምን ያህል እንደተጐዱና እንደተከፉ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህንንም ደራሲው ሲያረጋግጠው“አረንዛው በሼ እንኳን ከንጉስ ነገሥቱ የራስነት ስልጣን ማዕረግ እንዲወስድ ተጠርቶ ነበር፡፡ ግን በተፈሪ ጉዳይ እኩርፎ አዲስ አበባ ሲጠራ አልሄድም ብሎ እንጂ”. . .፡፡”/የጠፍ ከዋክብት፣234/ በመሆኑም የኪዳኔን የሹመት ልብሱን አስወልቀው ከገደሉ በኋላ የሹመት ልብሱን ጣሊያኖቹ የገደሏቸው ውሾቻቸው መቃብር ቦታ ላይ ሲያቃጥሉ እናያለን፡፡

ስለሆነም የአቶ በሼን ህሊናዊ መልክ ታሪኩ ከፋፍሎ ሊያሣየን ሞክሯል፡፡ አንደኛ ጣሊያኖችን ለማሣመን የሄዱበት መንገድ አሣማኝና ተቀባይነት ማግኘታቸው፣ ሁለተኛ ያገኙትን ተቀባይነት በመጠቀም በወኔና በታላቅ ሀገር ፍቅር ለአርበኞች ድጋፍ ማድረጋቸው፣በሶስተኛ ደረጃ ጥላቻንና ቂምን በማስወገድ ሰላምና ፍቅር ወዳድ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ በአራተኛ ደረጃ የሚወዷቸውን ሰው የገደሉ ብሎም ለመገደል ሰበብ የሆኑትን ሰዎች የተበቀሉ ሆኖው የተሣሉ ገፀባህሪይ ናቸው፡፡

### 3.2.2.5 የተፈሪ ህሊናዊ አሣሣል

ተፈሪ እንደሌሎች ገፀባህሪይ ሁሉ በህሊናዊ አሣሣል ልዩ ቦታ የተሰጠው ገፀባህሪይ ነው፡፡ ተፈሪ አስተዋይ ወጣት ለአገሩ፣ ለወገኑና ለእምነቱ ነፃ መውጣት “ወንዶች በረሃ” ገብቶ የሚዋጋ ለፍትህ የቆመ ፍርድ የሚሰጥ ሆኖ የተሣለ ገፀባህሪይ ነው፡፡ ከዚህ በመነሣት የተፈሪን ህሊናዊ አሣሣል ተንተን አርገን ለማየት እንሞክራለን፡፡

“ሰለ ተፈሪ፣ በተፈሪ ስም! ....” ከተባለ ምንም ህገወጥ ሥራ አይሠራም፡፡ አውሮፓውያኑ ህጋዊ አስተዳዳሪ እኛ ነን ይበሉ እንጂ ጅሩና ተጉለት እንደሆነ የሚተዳደረው በተፈሪ ስም ነው/ የጠፍ ከዋክብት፣27/ ከዚህ ሃሣብ እንደምንረዳው ምን ያህል ሃያል እንደሆነና ለፍትህ እንደቆመ የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም እንዲህ ብሎ ያጠናክረዋል፡፡ ማንም “በተፈሪ ስም” ተብሎ ህገወጥ ነገር ቢሰራ የተፈሪ ነበልባል ክንዶች አይምሩትም ይቀጡታል፡፡ ተፈሪ ቅጣትን በተመለከተ ወደ ኋላ የሚል ልብ የለውም / የጠፍ ከዋክብት፣27/ ስለዚህ ተፈሪ ለነፃነት ከሚያደርገው ትግል ባሻገር በአካባቢው ያለውንና የሚሠራውን ግፍ ሲከላከል ብሎም እርምጃ ሲወስድ ይስተዋላል፡፡ ይህንንም ፍርድ ሲሰጥ ደራሲው እንዲህ ሲል ያስነብበናል፡፡‹‹. . . አንድ ሺፍታ ነኝ ባይ ሰው የአንድ ገበሬ ሚስት ገብቶ ደፈራት የሰውየውንም ከብቶች ጥርግርግ አድርጐ ነዳቸው፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ተመልሶ መጣና የገበሬውን በጎች ሊነዳ ሲሰናዳ ብሶት የገባው ገበሬ “በጎቼን ብትነዳቸው ግን ተፈሪን እንደደፈርህ ቁጠረው በተፈሪ ስም

ብየኀለሁ!» ሲል ተናገረው፡፡ /የጠፍ ከዋክብት፣28/ ሽፍታው በመናደድ ተፈሪን አለመፍራቱን አንተን በመግደል አረጋግጥለታለሁ በማለት ገበሬውን ገሎ ሚስቱንና በጎቹን ይዞ ሄደ፡፡

> ተፈሪ ፍርድ ሰጠ፡፡ ሽፍታውን ከመግደሉ በፊት ከሰዎች ሁሉ የወሰደውን እንዲመልስ አደረገው፡፡ ከዚያም ህዝብ በተሰበሰበበት በፅኑ ገረፈው ፡፡ በመጨረሻም በህዝብ ፊት ግንባሩን ብሎ ደፋው . . . ስቃዩ እንዲጠነከረበትና መቀጣጫ እንዲሆን ተፈሪ በጥበበኛ ባሠራው እየተወረወረና እየወጋ በሚቀረድድ መሣሪያ እንጂ፡፡/የጠፍ ከዋክብት፣28/

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለሀገሩ ነፃ መውጣት የሚያደርገው የጀግንነት ጉዞ እንደሚከተለው ይተነተናል፡፡ ለዚህ የጀግንነት ጉዞው ደግሞ ግንባር ቀደም ተዋጊ ከመሆኑም ባሻገር ጦሩን የማስተባበር ብሎም ለነፃነት ማንም አዛዥና ታዛዥ የለም የሚለው ፍልስፍና ነው፡፡ ደራሲው ይህንን እንዲህ ሲል ፅፋል፡፡ “የተፈሪ መሪነት በራሱ ልዩ ነው፡፡ ከማንኛውም መሪ አመራር የሚደነቅበትና የሚወደስበት ዘይቤ አለው፡፡ ሌሎች መሪዎች ቀድመውን ዘለው ጦርነት ውስጥ አይገቡም፡፡ እርሱ ግን ዘሎ እራሱ ይፈፀማል”፡፡/የጠፍ ከዋክብት፣88/ ከዚህ እንደምንረዳው ፊት ቀድሞ የሚገኘው ተፈሪ መሆኑን ነው፡፡ አንድ ድርጊት ፈፅሞ የሚያስፈፅም ጠንካራ ሰው መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም እንዲህ ሲል ይደመጣል፡፡

> “እዚህ ማንኛችንም ከማንኛችን መመሪያ አንጠብቅም አሁን አገሪቱ እንኳ ንጉስ አልባ ሆናለች፡፡ ንጉስ ተብዬውም ጥላት ፈርጥጧል አሁን የሚመራን የሌላ ህዝቦች ሆነናል ስለዚህ እያንዳንዳችን እራሣችንን መምራት፣ ማስተባበር አለብን እንደገናም እያንዳንዳችን በእያንዳንዳችን መመራት አለብን፡፡›› /የጠፍ ከዋክብት፣88/
>
> “ይህ ነው በተፈሪ ጦር ውስጥ ያለው ዕሣቤ፡፡ ይሄን ዕሣቤ የተማረው ደግሞ ከራሱ የህይወት ገጠመኝ ነው፡፡ ሲሸፍት ሲወጣ የተከተሉት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡ አሁን ሁለቱም ሞተዋል ወራት ባልሞላ ጊዜ ግን በሺዎች የሚቆጠሩ ተከታዮችን አፈራ”/የጠፍ ከዋክብት፣88/

ከጥቅሱ እንደምንረዳው የጀግንነቱ መሠረት የማስተባበር ልዩ ችሎታው እንደሆነ ግልፅ ነው ለዚህም ግምባር ቀደም ተዋጊና ጀግና መሆኑን የራሱ አርበኛ ጓደኞችና ወራሪዎቹ በሚገባ የሚገነዘቡት ጉዳይ ነው፡፡ ይህንንም እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል፡፡“. . . ይሄ ተፈሪ የጦር ወሬ ሲሰማ መላእክት በእጆቻቸው ይዘው በአየር ላይ የሚያንሣፍፉት

ይመስል ሊደርሱበት አለመቻሉ ይገርማል፡፡ እናም ከአውሎ ነፋስ እንኳ ይቀድማል፡፡ ገደሉን፣ ጥሻውን፣ አቀበቱንና ከፊቱ ያገኘውን አስቸጋሪ ነገር ሁሉ እንደ አስደሣች አልጋ ይጨፍርበታል አለ ፍኖተአብ፡፡"/የጠፍ ከዋክብት፣89/ ይህ ጓደኞቹ ስለ ጀግንነቱና ስለተዋጊነቱ የገለጹት ሲሆን፡፡ የጣሊያኑ ጄነራል ስለ ተፈሪ እንዲህ ሲል ይደመጣል፡፡

> "ይህን እንደተዋጊ ፈረስ ጦርነት ውስጥ ሲሆን፣ የጦርነት ሽታ ሲሸተው፣ የባሩድ ጭስ ሲያጥነው፣ የጠላት መአት ሲከበው . . . ወደፊት ወደ ጠላቱ ግንባር የሚገሰግስ የጦር ሰው እውነትም እንደ ሰሙ ተፈሪ እና ኃያል ጦረኛ መሆኑን ጠላቶቹ ተረድተውታል፡፡ ጄነራል ፍራንኮ እንኳን ሳይወድ በግድ "ያ! ተፈሪ የሚባል እንደ ሰሙ የሚያስፈራ ጀግና" ይለዋል ስለ ተፈሪ መናገር ሲጀምር፡፡" /የጠፍ ከዋክብት፣75/

ከዚህም በተጨማሪ ተፈሪ በህሊናዊ አሣሣል ሐይማኖትኛነቱንና ለሃይማኖቱ ተቆርቋሪ ሆኖ እናገኘዋለን ሲደሰት ወይ ሲከፋው የሚያደርገው የተለየ ነገር አለ፡፡ ይኸውም ከፈጣሪ ጋር ለመለማመን ቅዱስ መጽሐፍት ያነባል ይህንንም ደራሲው እንዲህ ይገልጸዋል፡፡ ቀስ ብሎ ወደ መፃህፍቱ ሄደ፡፡ እናም ትልቁን በግዕዝ የተፃፈውን ቅዱስ መፃህፍ አነሣ፡፡ ‹‹…ቀስ ብሎም አገላበጠው፡፡›› /የጠፍ ከዋክብት፣105/ ከዚህ እንደምንረዳው ምን ያህል ሃይማኖተኛ መሆኑን ጣሊያን የኦርቶዶክስ እምነት ለማጥፋትና የነሱን እምነት ለማስፋፋት በሚያደርገው ጥረት የእምነቷን መገልገያ የሆኑትን ቁሶች በማቃጠልና በማውደም ሥራ በመጠመድ ተፈሪም ሃይማኖቱንና መገልገያ ቁሶቿን ለመታደግ ያደረገውን ጥረት ደራሲው እንዲህ ጽፎታል

> ‹‹ ተፈሪ ለዚህ ህዝብ ትልቅ ጥላ ሆኖለታል ለቤተክርስቲያኑቱም ከለላ ሆኖለታል ቅዱሣን እቃዎቿን ይደብቅላታል፡፡ጠላቶች ቤተክርስቲ ያኑቱን ከበው በሚያቃጥሉበት ጊዜ አደጋ እየጣለ፣ፊት ለፊት እየገጠመ ቁም ስቅላቸውን አሣይቷቸዋል፡፡"/የጠፍ ከዋክብት፣178/፡፡

ከዚህም ሌላ ተፈሪ አስተዋይና ሠላም ፈላጊ እንደሆነ ታሪኩ ያስረዳናል፡፡ በአንድ ወቅት ባለቤቷ የሞተባት ሴትን ባልሽን የገደሉት የጠገናው የልጅ ልጆች ናቸው ተብሎ በመወራቱ እነሱ አለመግደላቸውንና አላግባብ ደም መፋሰስና ቁርሾ እንዳይኖር ያደረገውን ጥረት ደራሲው እንዲህ ገልጾታል፡፡"...ከእኛ ቤት ማንም ባለቤትሽን እንዳልነካው ሁሉም ሊምሉልሽ ይችላሉ በኛ መካከል ቁርሾ ሣይሆን ዝመድና እንዲኖር

እፈልጋለሁ፡፡ በመሆኑም አበልጅ እንድንሆን ስለምፈልግ ልጅሽን ክርስትና ላንሣው" . ..፡፡"/የጠፍ ከዋክብት፣129/ ብሎ የተናገረው ሰላም ፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር ለአስተዋይነቱ ምስክር ነው፡፡ ይህንንም ሃሣብ ለማጠናከር ባሏ የሞተባት ሴት እንዲህ ስትል ተጽፉል ". . . ጨዋነቱን እኔ እራሴ አውቃለሁ. . .ክርስትና ላንሣው ብሎ የመጣ ጊዜ ነው ትልቅና አስተዋይ ሰው እንደሚሆን የተረዳሁት . ."/የጠፍ ከዋክብት፣129/ እናም ይህ ባህሪይው ከልጅነቱ ጀምሮ አብሮት ያደገና የጨዋ ባህሪይ የተላበሰ ተደርጎ የተፃፈ ነው፡፡

3.2.2.6 የኪዳኔ ህሊናዊ አሣሣል

አቶ ኪዳኔ ኢትዮጵያ በጣሊያንን በተወረረችበት ወቅት ከጣሊያን የወገነ ባንዳ ሆኖ የተሣለ ገፀ ባህሪይ ነው፡፡ ባንዳ እንዲሆን የገፋፋው ነገር ደግሞ ለበቀል፣ ካለው ፍላጎት በራስ አለመተማመን፣ ስልጣን ወዳድ መሆኑና ፈሪነቱ ነው፡፡ ከነዚህ ባህሪው በመነሣት በቀለኝነቱን እንተነትናለን፡፡ በተለይ አቶ በሼንና ቤተሰቦቻቸው ላይ ጐልቶ የሚታየው የበቀለኝነት መንፈስ በሴማዊት ምክንያት መሆኑን ታሪኩ እንዲህ ያስረዳናል፡፡"... አቶ ኪዳኔ ከአምስት አመት በፊት ሴማዊትን እንዲድሩለት ይጠይቃል፡፡ የአቶ በሼ ቤተሰብ ግን‹‹ እነ ኪዳኔ ቁምጥና ስለአለባቸው ለእርሱ አንድርም፡፡" አሉ /የጠፍ ከዋክብት፣30/ በዚህ የተነሣ ከጣሊያን በመወገን ለአገርና ለወገን ተቆርቋሪ የሆኑትን በሼንና ቤተሰባቸውን ለመበቀል ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር ግንኙነት ያላቸው የሮማ መንግስት ጠላቶች ናቸው በማለት ለማጋለጥ የሚያደርገውን ትግል ደራሲው እንዲህ ይገልፀዋል፡፡

> አቶ ኪዳኔ በሼን ትክ ብሎ ሲያያቸው ከቆየ በኂላ ለራሱ በተገርሞ እንዲህ አለ . . . ጠላቴ ባይሆን ኖሮ ጥሩ ነበር አሁን ግን አንዴ ጠላት ሆነናል፡፡ ካሁን በኂላ ደስተኛ ልሆን የምችለው ነገር ቢኖር እንደዚህ አይነቱን ሀይለኛና ጠንካራ ጠላቴን ማሸነፍ ከቻልኩ ብቻ ነው . . . "/የጠፍ ከዋክብት፣31/

በዚህ ብቻ አላበቃም ምንም እንኳ አቶ በሼንና ዘመዶቻቸውን ለማጋለጥ ያደረገው ሙከራ ባይሣካለትም የበሼን እህት የተፈሪን እናት እንዲገድል ከጣሊያኑ ጀነራል ፍራንኮ ትዕዛዝ ሲሰጠው ያለውን እንደ አብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡"ኪዳኔ ፊቱ እንደ ብርሃን በራ፡፡ "የተፈሪን እናት መግደል እንዴት ግሩም ደስታ ይሰጣል፡፡ መግደል እናቶችን ነው እንጂ ጀግና እንዳይወለዱ . . . ፡፡"ሲል ተፈላሰፈ /የጠፍ ከዋክብት218/ ተፈላስፎ ብቻ አልቀረም የተፈሪን እናት "አስካለ ማርያምን በብረትምጣድ እየተጠበሰች

ሳለ ኪዳኔ ደጋግሞ በጥይት ደበደባት፡፡" ከዚህ የምንረዳው ኪዳኔ ምንም ርህራሄ የሌለው የበቀል ጥም ያሰከረው ሰው መሆኑን ነው፡፡

ኪዳኔ ከተፈሪ እናት በተጨማሪም ይጠነቁልለት የነበረው ጉምዴን በመጥረቢያ አንገቱን ሲቆርጠው ታሪኩ ይነግረናል፡፡ ይህንንም ያደረገው ጠንቋዩ በገዛ ፈቃዱ ለኪዳኔ አልጠነቁልም በማለቱና በጠንቋይ በመሰደቡ የኋላ ኋላ መታለሉ ስለገባው ነው፡፡ ደራሲውም እንዲህ ይገልፀዋል፡፡"ንዴቱን ለመወጣት ደግሞ እጉምዴ ላይ አፍጥጦ ጮኸበት፡፡ "አንተ ውሻ አታለልከኝ አይደል? እበቀልሃለሁ፡፡" ብሎ መጥረቢያውን ከፍ አድርጐ ያዘ፡፡" /የጠፍ ከዋክብት፣209/ በዚህ ብቻ ሣይቆም አንገቱን እንዴት እንደቆረጠው እንዲህ ይገልፃል፡፡

> "አቶ ኪዳኔ መጥረብያውን ወደ ጉምዴ አንገት ሠነዘረው፡፡አቶ ኪዳኔ መጥረቢያውን ሲሰነዝር ጉምዴ መሣቅ ጀመረ፡፡ "አሃሃሃሃ . . . አሃሃሃ. .. "አንገቱ ለብቻው ቁር ብሎ ሄደ አንገቱመ ለብቻው ተቀንጥሶ እወደቀበት መሣቁን ቀጠለ . . .፡፡"/የጠፍ ከዋክብት፣210/

ከጥቅሱ የምንረዳው ምን ያህል ጨካኝና በቀለኛ መሆኑን ነው፡፡ ከዚሁ ጐን ለጐን ለስልጣን ካለው ፍቅር የተነሣ ከጣሊያኖች ሽልማትና ሹመት ለማግኘት ጉምዴ የተባለ ጠንቋይ እቤቱ በማስቀመጥ ሲያስጠነቁል እናገኘዋለን፡፡በዚህም ምክንያት በጠንቋይ ትዕዛዝ መሠረት ሰው እስከመግደል የደረሰ ስልጣንና ዝና ያስከረው መሆኑን ታሪኩ እንዲህ ይነግረናል፡፡

> "አቶ ኪዳኔ እንደለመደው በግንባሩ ተደፋ፡፡ . . . እንዲህ ሲል ተማፀነ እጉምዴ ላይ የሰፈሩትን አጋንንቶች የወደፊት እድሎን እንዴት እንደሚቀና ጠላቶቼ እንዴት እንደሚጠፉ እና የጣሊያን መንግስት እንዴት ወዳጅ ሊሆነኝ እንደሚችል ስልቱን ይነግረኝ ዘንድ እማፀናለሁ /የጠፍ ከዋክብት፣47/

የዚህ መልክዕክት በዋናነት ዕድሉን፣ አቃንቶ፣ ጠላቶቹን አጥፍቶ፣ የጣሊያን መንግስት ይሁንታን አግኝቶ ሹም ለመሆን ያለውን ፍላጐት እንድንረዳ ያደርገናል፡፡ ሌላው የኪዳኔ ሰብዕና ፊሪ፣ ነገሮችን ፊት ለፊት የማይጋፈጥና በራሱ የማይተማመን ሆኖ ተስሏል፡፡ ይህንንም ሚስቱ የነበረችው የዝማ እና ቤቱ ያስቀመጠው ጠንቋይ ጉምዴ እንዲህ ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ ". . . ይሄን ወኔ ቢስ በራሱ የማይተማመን ባል አግብቼ እንዲህ ልቃጠል . . . ›/የጠፍ ከዋክብት ፣45/ ስትል እንሰማታለን፡፡

በተጨማሪም ጉመዴ የተባለው ጠንቋዩ ደግሞ እንዲህ ይጋልፀዋል፡፡ አቶ ኪዳኔ ሲታሰበው ደግሞ ለኪዳኔ አፈረለት፡፡ ሁልጊዜ ሽንባና ፊር ሰዎች አለምን ፊት ለፊት መግጠም ስለሚሣናቸው በእጅ አዙርና በጥንቆላ ሊያሸንፉት ይታገላሉ፡፡ . . /የጠፍ ከዋክብት ፣204/ ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው የኪዳኔ የህሊናዊ መልኮች ጥሩ ሆነው ያልተሣሉ በገሀዱ አለምም የሚታዩና ሊገኙ የሚችሉ ሆነው የተቀረፁ ናቸው፡፡

3.3 ማጠቃለያ

የጠፍ ከዋክብት ረዥም ልቦለድ ውስጥ ያሉትን ስድስት ዋናዋና ገፀ ባህሪያት አካላዊና ህሊናዊ አሳሳላቸውን ተመልክቻለሁ፡፡

አብዛኛዎቹ ገፀባህሪያት በውጫዊ ማንነታቸው የገሃዱ አለም ሰዎችን የሚመስል አለባበስ፣ ተክለሰውነት፣ ስያሜ፣ ይዘው የተቀረፁ ናቸው፡፡ ምንም እንኳ ውጫዊ መልካቸው በተለይ ከአንዷ ገፀባህሪ በቀር አለባበሳቸው ተንተን ተደርገው ባለመቅረባቸውና በተለያየ ቦታ አንድ አይነት የሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረጋቸው ገፀባህሪያቱ ምንም አዲስ ነገር ሲያደርጉ አለመታየታቸው ለተደራሲ ሳቢነት እንዳይኖረው አድርጎታል፡፡

ከዚህም ሌላ ደራሲው የኪዳኔን ውጫዊ መልክ ተንትኖ ሳይገልጽ በስም ብቻ አስተዋውቆን ማለፉ አንባቢ ምስል እንዳይከስትለትና ከሌሎቹ ገፀባህሪያት እንዳይለይ አድርጓታል፡፡ እንዲሁም የጄነራል ፍራንኮንና የምክትል ጄነራል ሲልቪዮን አካላዊ ገለፃ በአንድ ላይና በአንድ ቦታ መቅረጹ ለተደራሲ ብዥታ የሚፈጥር ከመሆኑም ባሻገር ጄነራል ፍራንኮ ይኸን ይመስላላ፣ ምክትል ጄነራል ሲልቪዮ ይኸንን ይመስላል ለማለት የማያስችል በመሆኑ የታሪኩን አጓጊነት የሚቀንሰው በመሆኑ እንደድክመት የሚጠቀስ ነው፡፡በአጠቃላይ ደራሲው በአካላዊ ገለፃ በኩል ሰፊ ክፍተትና ጉድለት ታይተውበታል፡፡

ሌላው ገፀባህሪያቱ በውስጣዊ ማንነታቸው ሰዋዊ ባህሪያትን የተጎናፀፉ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ገፀባህሪ ለአላማቸው መሳካት በሚያደርጉት ፍትጊያ አንዱ ከሌላውጋ ሲጋጭ ፣ሲፋቀር ወይም ሲመካከር ይስተዋላል፡፡የተሰጣቸውንም ሥነ ምግባር፣ ዕምነትና ሞራል ወዘተ. . . አንዱን ገፀ ባህሪ ከሌላው እንድንለየው ከማስቻሉም በላይ በገሃዱ አለም ያሉ ሰዎች የተለያዩ የሕይወት ገጽታዎች እንዳሏቸው የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ስለዚህም ከአካላዊ ገለፃ የተሻለ ትንታኔ የተሰጠበትና የደራሲው ጠንካራ ጎኑ የታየበት ነው ፡፡

በአጠቃላይ ልቦለዱ ከአማርኛ ልቦለድ ዕድገት አንፃር ሲፈተሽ ጥሩ ሥራ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደተጠቀሰው ገፀባህሪያቱ አካላዊ መልካቸው በአግባቡ የተቀረጸ ባለመሆኑ ትልቅ ክፍተት አሳይቷልና፡፡

<u>**ዋቢ ጽሑፎች**</u>


ሽንቁጥ አየለ፤<u>የጠፍ ክዋክብት</u>፡፡ አዲስ አበባ፤ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1999 ዓ.ም

ሽባባው ወሌ፤ "የጭብጥ፣ የግጭትና የገፀ ባህርያት ትንተና **<u>በአደፍርስ</u>**ና **<u>ከአድማስ ባሻገር</u>** ውስጥ"፡፡ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 1976 ዓ.ም ፡፡/ዲማጽ/

አማረ ማሞ፤ *<u>የልቦለድ ድርሰት አፃፃፍ መሠረታዊ መመሪያ</u>* ፡፡ አዲስ አበባ፤ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1968፡፡

ደሳለኝ አሰፋ፤ "ሥነ ፍሑፋዊ ሂስ **<u>በኢቫንጋዲ</u>** እና **<u>ከቡስካ በስተጀርባ፡፡</u>** የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡ 1992 ዓ.ም ፡፡ /ዲማጽ/

ዘሪሁን አስፋው፤ <u>የስነፍሑፍ መሰረታውያን፡፡</u> አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት ፣ 1992 ዓ.ም፡፡

ዮሴፍ ጌትነት፤ ‹‹ ሽፍትነት **<u>በጥቁር ደም</u>** ልቦለድ የገፀ ባህርያት አቀራረጽ››፡፡ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም አዲስ አበባ የኒቨርስቲ፣ 1993 ዓ.ም፡፡ /ዲማጽ/

ፋንታሁን እንግዳ፤ **<u>ዝክረ ተውኔት፡፡</u>** አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም፡፡

Bames,Michael H: in the presence of mystry: An introduction to the story of <u>Human Religiousness</u> tewenty-third pub's 1990

Harry Show: <u>Dictionary of literary Tems</u> New york .Mc graw Hill book campany,1992

PickeringJames H:<u>Literature</u> 5th ed USA prentice Hall inc;1997 Psycholgy:1997